# የቅጥር መግለጫ መመሪያ

## ለግለሰብ አገልገሎት ሰጪዎች



Washington State Department of Social & Health Services

*Transforming lives*

# የርዕስ ማውጫ

## መግቢያ


የቅጥር መግለጫ መምሪያ አጠቃቀም ለግለሰብ አገልገሎት ሰጪዎች ........ 1

የአገልግሎት ተቀጣሪዎች አለማቀፋዊ ህብረት 775 ........ 1


## የቅጥር ሂደት


ቀጣሪዎት ........ 2

የቅጥር መሰረታዊ ሁኔታዎች ........ 2

የኋላ ታሪክ ምርመራዎች ........ 3

የ DSHS ውል መፈረም ........ 5


## የስልጠና እና የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ (HCA) ማረጋገጫ መስፈርት


የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ (HCA) ማረጋገጫ ........ 6

መግለጫ እና የደህንነት ስልጠና ........ 7

የ70 ሰአታት ስልጠና መስፈርት ........ 8

ከ70 ሰአታት ስልጠና እና የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ (HCA) ማረጋገጫ ነጻ መደረግ ........ 9

ለወላጅዎ ወይም ለልጅዎ አገልገሎት የሚሰጡ ከሆነ ........ 10

ለአንድ ሰው ብቻ እንክብካቤ የሚሰጡ ከሆነ፣ በወር 20 ሰአታት ወይም ከዛ በታች ........ 10

የስልጠና እና/ወይም የማረጋገጫ የጊዜ ገደብ የማያከብሩ ለሆነ ........ 11

ወደስራ መመለስ ........ 11

የነርስ ተልዕኮ መስፈርቶች ........ 12

ቀጣይ የትምህርት መስፈርቶች ........ 12

የረዥም-ጊዜ የእንክብካቤ ሰራተኛ ስለጠና መስፈርቶች ቻርት ........ 13

የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ዝርዝር ለግለሰብ አገልግሎት ሰጪዎች ........ 15


## ክፍያ ስለማግኘት


የግለሰብ ProviderOne መግቢያ ........ 19

ክፍያ ያለው ፈቃድ (PTO) ሰአታት ........ 21

የስልጠና ሰአታት ........ 22

የትርፍ ሰአት ስራ ክፍያ እና ስራ ሳምንት ገደብ ........ 22

የጉዞ ሰአት ........ 25

የጉዞ ካሳ ክፍያ ........ 28

ደሞዞች እና የክፍያ ጭማሪዎች ........ 28

**ተቀናሽ ግብር እና ክፍያ**


የፌደራል የገቢ ግብር መያዝ .......... 29

የ W-2 ደሞዝ መግለጫ .......... 31

የማህበራዊ ደህንነት እና Medicare ግብር .......... 32


**አጠቃላይ የቅጥር መረጃ**


የጤና መድህን አማራጮች .......... 33

ጡረታ .......... 35

ተጨማሪ ደንበኛ ማግኘት .......... 35

የሰራተኛ ካሳ .......... 36

ጥቅማዎች፣ የቅጥር ማረጋገጫ፣ የገቢ ማስረጃ .......... 37

ስራዎትን ቢለቁ .......... 38

የስራ አጥነት ጥቅማ-ጥቅሞች .......... 38


**ጥቃትን የማሳወቅ ግዴታ**


ለጥቃት የተጋለጠ አአዋቂ ሰው ማን ነው? .......... 39

ጥቃት ምንድን ነው? .......... 39

አለ ተብሎ የሚገመትን ጥቃት ማሳወቅ .......... 40

እንክብካቤ ስለሚሰጥ ቦታ ያሉ ስጋቶችን ማሳወቅ .......... 41

**ለመረጃ እና ግብአት ፈጣን መመሪያ** .......... 41



## መግቢያ

### የቅጥር መግለጫ መምሪያ አጠቃቀም ለግለሰብ አገልገሎት ሰጪዎች(IPዎች)

ወደ አዲሱ የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ (IP) ስራዎት እንኳን በደህና መጡ፡፡ ስራዎት አስፈላጊ ነው፡፡ የሚሰጡት እንክብካቤ የቀጣሪዎትን ደህንነት ይደግፋል እንዲሁም ቀጣሪዎት በተቻለው መጠን ራሱን ችሎ እንዲኖር ያግዛል፡፡

ይህ መመሪያ ስለእርስዎ የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ቅጥር መረጃ አለው፡፡ በዚህ መመሪያ የሚካተቱ ሌሎች አስፈላጊ ርዕሶችን ለማየት የማውጫ ሰንጠረዡን ያንብቡ፡፡ ይህን መመሪያ የሚያገኙበት ቦታ ያስቀምጡት እና ለመረጃ እና አድራሻ ይጠቀሙት፡፡

### የአገልግሎት ተቀጣሪዎች አለማቀፋዊ ህብረት 775

ሁሉም ግለሰብ አገልግሎት ሰጪ የረዥም ጊዜ የእንክብካቤ ሰራተኞች በአገልግሎት ተቀጣሪዎች አለማቀፋዊ ህብረት (SEIU) 775 ይወከላሉ፡፡ ይህ የሆነው በግለሰብ አገልገሎት ሰጪዎች በ2002 ህብረት ለማቋቋም ባደረጉት አብላጫ ምርጫ ነው፡፡ በህብረት መወከል ማለት ህብረቱ ስለጥቅማ-ጥቅም እና የስራ ሁኔታ በ IPው ስም ይደራደራል፤ ይህም የህብረት የመደራደሪያ ስምምነትን (CBA) ይፈጥራል፡፡ CBA በየሁለት አመቱ ድርድር ይደረግበታል፡፡

አዳዲስ IPዎች በመጀመሪያ የመወያያ ሂደት ወቅት፣ መሰረታዊ ስልጠና ሲሰጣቸው እና ከዛም በመቀጠል የሚኖር አንዳንድ ትምህርቶች ወቅት የህብረቱን ተወካይ የሚያገኙበት እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ከህብረቱ ተወካይ ጋር መገናኘት በእያንዳንዱ IP ፈቃደኝነት ነው፡፡

አሁን ያለውን የ CBA ቅጂ የሂሳብ አስተዳደር ጽ/ቤት (OFM) በመሄድ ኦንላይን www.ofm.wa.gov ላይ የህብረት የመደራደሪያ ስምምነትን የሚለውን በመምረጥ ማየት ይችለሉ፡፡ ስለክፍያ መጠን፣ ስለደሞዝ ጭማሬ፣ ስለቅጥር ጥቅማ-ጥቅምዎት ዝርዝር መረጃ ይገኛል፡፡

ስለህብረት ድርድር ስምምነት፣ ህብረት፣ የህብረት አባልነት፣ የህብረት ጥቅም ወይም ፈቃደኝነት የህብረት ስራዎችን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት የአባል ምንጭ ማዕከል **1-866-371-3200** ጋር ይደውሉ፡፡

ስለ CBA ወይም የህብረት አባልነት ጥያቄ ካለ IPዎች SEIU 775 ነጻ መስመር በአባል የግብአት ማዕከል 1-866-371-3200 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ በ8AM-6PM ማነጋገር ይችላሉ፡፡

# የቅጥር ሂደት

## ቀጣሪዎት

በዚህ መጽሄት ላይ "ቀጣሪ" የምንለው የእንክብካቤ አገልገሎት የሚሰጡትን ሰው ነው፡፡ የእንክብካቤ አገልገሎት የሚሰጡትን ሰው እንደቀጣሪዎት በመሆን ይቀጥርዎታል፣ ስራዎትን ይመራል፣ ይቆጣጠርዎታል እና የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች እንዴት እንደሚሰጡ ይወስናል ማለትም በሚፈቀድልዎት የስራ ሳምንት ሰአት ገደብ ውስጥ የሆነ አገልገሎት አሰጣጥ ፕሮግራም ያወጣል፡፡ እንዲሁም ሊያባርርዎት/ልታባርርዎት ይችላሉ፡፡

ቀጣሪዎት የማህበራዊ እና ጤና አገልግሎቶች መምሪያ (DSHS) ደንበኛ ነው፡፡ የሚሰጡትን አገልግሎት DSHS ያስተባብራል እንዲሁም ይከፍላል፡፡ ቀጣሪዎት ከDSHS ጋር ስላለው ግንኙነት ስናወራ የDSHS ደንበኛ ብለን እንጠራዋለን፡፡

ቀጣሪዎት ማለት የእንክብካቤ አገልግሎት የሚሰጡት ሰው ማለት ነው፡፡

## የቅጥር መሰረታዊ ሁኔታዎች

DSHS ግለሰብ አገልገሎት ሰጪ ሆነው ለመስራት ክፍያ የማይፈጽምበት አጋጣሚዎች አሉ፡፡

ለምሳሌ በሚከተሉት ምክንያቶች ግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ሆነው አይከፈልዎትም፡

- ለባለቤትዎት የሚከፈለው እንክብካቤ ሰጪ መሆን ከፈለጉ፡፡
- የሚከፈለው እንክብካቤ የሚያስፈልገው እድሜው አስራሰባት ወይም ከዛ በታች የሆነ ልጅ ባለጉዳይ የተፈጥሮ፣ የእንጀራ ወይም የጉዲፈቻ ወላጅ ከሆኑ፡፡
- የሚከፈለው እንክብካቤ የሚያስፈልገው ልጅ በእርስዎ ፈቃድ ባለው ማደጎ ቤት ውስጥ እንክብካቤ የሚሰጡት የማደጎ ወላጅ ከሆኑ

እነዚህ ሁኔታዎች የማይመለከትዎት ከሆነ የግል አገልገሎት ሰጪ ሆነው DSHS ክፍያ እንዲፈጽምልዎት በቀጣይነት ማሟላት ያለብዎት ብዙ መስፈርቶች አሉ፡፡

ብቁ መሆን አብዎት፡፡ ይህ ማለት፡

- 18 አመት እድሜ እና ከዛ በላይ መሆን አለብዎት
- አስፈላጊውን የኋላ ታሪክ ሂደት ማጠናቀቅ እና በውጤቶቹ ማለፍ መቻል
- በባህሪይ በብቃት እና ምቹነት ረገድ ከልጆች እና ለጉዳት ተጋላጭ ከሆኑ አዋቂ ሰዎች ጋር ገደብ የለሽ የቆይታ ጊዜ ማድረግ መቻል
- የግለሰብ እንክብካቤ አገልግሎቶች ለመስጠት የሚያስፈልገው የቤት እና ማህበረሰብ አገልገሎቶች/የእድገት ውስኑነት አስተዳደር ግለሰብ አገልግሎት ሰጪ አገልገሎቶች ውልን ከ DSHS ጋር ለማድረግ ብቁ መሆን እና መፈረም፣ በውስጡ በተካተቱት ሁኔታዎች መስማማት እና የውሉን ደንቦች ሁሉ ማክበር፡፡
- ስልጠና ማጠናቀቅ እና የማረጋገጫ መስፈርቶች፡፡
- የተከለከለ፣ የታገደ ወይም የተሰረዘ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ማረጋገጫ የሌለው፡፡

ይህ አጠቃላይ ዝርዝር አይደለም፤ ማሟላት ያለብዎት ሌሎች መስፈርቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

## የኋላ ታሪክ ምርመራዎች

### ስለመጀመር

ግለሰብ አገልግሎት ሰጪዎች ውለ ከማድረጋቸው በፊት የ Washington ግዛት የኋላ ታሪክ ምርመራን ማለፍ አለባቸው እንዲሁም በተቀጠሩ በ120 ቀናት ውስጥ የ FBI የጣት አሻራ የኋላ ታሪክ ምርመራን ማድረግ አለባቸው። የ Washington ግዛት የኋላ ታሪክ ምርመራን ቢያንስ በየሁለት አመቱ ማድረግ አለብዎት እንዲሁም የክልል የጣት አሻራ የኋላ ታሪክ ምርመራን መምሪያው በጠየቀ ወቅት ማድረግ አለብዎት።

የኋላ ታሪክ ምርመራ ሂደቱን ለመጀመር ኦንላይን የኋላ ታሪክ ምርመራ ፈቃድ ቅጽ አግኝተው ይሞላሉ። ቅጹ ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች በሙሉ እውነተኛ መልስ መስጠት አለብዎት። የኦንላይን ቅጹን ከሞሉ በኋላ የማረጋገጫ ኮዱን ይጻፉ። ይህን ኮድ የተሞላውን የኋላ ታሪክ ምርመራ ቅጽ ለማግኘት እና ለማስገባት DSHS ይፈልገዋል።

የ Washington ግዛት የኋላ ታሪክ ምርመራ ካለፉ ለጣት አሻራዎት ቀጠሮ የሚያስይዝ እና ምን ይዘው መምጣት እንዳለብዎት የሚገልጽ መመሪያ ይደርስዎታል።

ወዲያው ቀጠሮ ማስያዝ አስፈላጊ ነው። በተቀጠሩ በ120 ቀናት ውስጥ ውጤቱ DSHS ጋር ካልመጣ እስኪመጣ ድረስ እንዲሰሩ አይፈቀድልዎትም።

የኋላ ታሪክ ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ የኋላ ታሪክ ምርመራውን ካደረገው ጽ/ቤት የውጤትዎን ቅጂ ማግኘት አለብዎት። የኋላ ታሪክ ምርመራ ውጤቱን መሀደርዎት ውስጥ ያስቀምጡት! ስለኋላ ታሪክ ምርመራዎት ተጨማሪ መረጃ ወይም ከኋላ ታሪክ ምርመራ ማዕከላዊ ቡድን የውጤትዎን ቅጂ በሚከተለው መጠየቅ ይችላሉ፡

ስልክ (360) 902-0299
ፋክስ (360) 902-0292
ለBCCUInquiry@dshs.wa.gov ኢ-ሜይል ያደርጉ



ውሉ በእርስዎ እና ስልጣን ባለው የ DSHS ተወካይ እስካልተፈረመ ድረስ ስራ ላይ አይውልም።

## የኋላ ታሪክ ምርመራ ውጤቶች

የኋላ ታሪክ ምርመራው ወንጀለኛነትን፣ ያልተቋጩ ክሶች ወይም ብቁ እንዳይሆኑ የሚያግዱ አሉታዊ እርምጃዎችን ከሳየ የግዛቱ ህግ ውል እንዲያደርጉም ሆነ በግዛት ወይም በፌደራል ገንዘብ እንዲከፈሉ አይፈቅድም።

ብቁ እንዳይሆኑ የሚያግዱ የጥፋተኝነት ወይም ያልተቋጩ ክሶች አንዳንድ ምሳሌዎች ጥፋት 1፣ 2 ወይም 3፣ ልጆች የሚፈጸም ወንጀል፣ ስርቆት 1 እና ዝርፊያ ናቸው። ሙሉው ዝርዝር WAC 388-113-0020 ላይ ይገኛል። ወንጀል ወይም ክስ ብቁ እንዳይሆኑ የሚያግግ መሆኑን ለማረጋገጥ ዝርዝሩን መልከቱ።

ብቁ እንዳይሆኑ የሚያግዱ አሉታዊ እርምጃዎች ምሳሌ ማለት መምሪያው፣ ፍርድቤት፣ የጤና መምሪያ ወይም ሌላ ቅጣት የሚተገብር ባለስልጣን የልጅ ወይም ለጥቃት ተጋላጭ የሆነ አዋቂ ሰው ጥቃት፣ መተው፣ ገንዘብ ምዝበራ ወይም ጉዳትን በተመለከተ የተረጋገጠ ግኝትን ያካትታል። ስለአሉታዊ እርምጃዎች ተጨማሪ መረጃ WAC 388-71 እና 388-825 ምዕራፎች ላይ ይገኛል።

ወዲያው ብቁ እንዳይሆኑ የሚያግዱ ሌላ የጥፋተኝነት ወይም ያልተቋጩ ክሶች ካለዎት በመሆኑም መምሪያው ከልጅ ወይም ለጥቃት ተጋላጭ ከሆነ አዋቂ ሰው ጋር መቆየት እንደማይችሉ ከወሰነ ክፍያዎት ወይም ውልዎት ይከለከላል ወይም ይቋረጣል።

## ባህሪይ፣ ብቃት እና ምቹነት (CC&S)

ባህሪይ፣ ብቃት እና ምቹነት መለያ ማለት ግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ከልጅ ወይም ለጥቃት ተጋላጭ ከሆነ አዋቂ ሰው ጋር ያለገደብ ለመቆየት የሚያስችለው ባህሪይ፣ ብቃት እና ምቹነት እንዳለው ለመወሰን መምሪያው የሚጠቀምበት የግምገማ ሂደት ነው።

መምሪያው ከልጅ ወይም ለጥቃት ተጋላጭ ከሆነ አዋቂ ሰው ጋር ያለገደብ ለመቆየት እንደማይችሉ ከወሰነ ክፍያዎት ወይም ውሎት ይከለከላል ወይም ይቋረጣል።

መምሪያው ከልጅ ወይም ለጥቃት ተጋላጭ ከሆነ አዋቂ ሰው ጋር ያለገደብ ለመቆየት እንደማይችሉ የሚወስንበት አንዳንድ ምክንያቶች የመጠጥ ወይም ሀሺሽ አላግባብ መጠቀም፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ወዲያው ብቁ እንዳይሆኑ የማያግዱ የጥፋተኝነት ወይም ያልተቋጩ ክሶች እና የደንበኛውን ፍላጎት የሚያሟላ በቂ አገልግሎት ለመስጠት አለመቻል ወይም ፈቃደኛ አለመሆን ወይም የደንበኛዎትን ጤና፣ ጥበቃ ወይም ደህንነት አደጋ ላይ መጣል ናቸው። ተጨማሪ መረጃ ማዕራፎች 388-71፣ 388-825 እና 388-113 WAC ላይ ይገኛል።

## የ DSHS ውል መፈረም

ግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ለመሆን የኋላ ታሪክ ምርመራ ካለፉ እና ብቁ ከሆኑ በኋላ ውል ለመፈጸም ለመምሪያው ትክክለኛ የማህበራዊ ደህንነት ካርድ፣ ፎቶ ያለበት መታወቂያ መስጠት እና የፌደራል የማግለያ ዝርዝር ምርመራን ማለፍ አለብዎት፡፡ ውልዎትን በየአራት አመቱ በሚያድሱበት ወቅት ሂደቱ ይህ ነው፡፡

ስራ ከመጀመርዎት እና ከመከፈልዎት በፊት የ DSHS ደንበኛ አገልገሎት ውል ይገመግሙ እና ይፈርማሉ፡፡ ውሉን በጥንቃቄ ይገምግሙት! የ ውሉ ለ DSHS ደንበኛ አገልግሎት በመስጠት እና ክፍያ ከ DSHS በመቀበል ምን ለማድረግ እንደተስማሙ ይዘረዝራል፡፡ የፈረሙትን ውል ደንቦች የማክበር ሀላፊነት አለብዎት እንዲሁም በዚህ የቅጥር መግለጫ መምሪያ መሰረት አገልግሎት መስጠት አለብዎት፡፡

ውሉን ከፈረሙ በኋላ ውሎት እና ይህ የቅጥር መግለጫ መምሪያ ብዙ ደንቦች እና ሁኔታዎችን ይይዛል፡፡ የውሉ እና መመሪያው ማስታወስ ያለብዎት አንዳንድ አስፈላጊ ደንቦች የሚከተሉት ናቸው፡

- በደንበኛው የአገልግሎት እቅድ የተካተቱ ፈቃድ ያላቸው አገልግሎቶች/ስራዎችን ደንበኛው በሚፈልገው መንገድ እና ምዕራፎች 388-71, 388-113, 388-114 እና 388-825 WAC ጨምሮ ተግባራዊ በሚደረጉ ደንቦች መሰረት ለመስራት ተስማምተዋል፣
- ደንበኛው ሆስፒታል፣ የእንክብካቤ ቤት፣ ICF/IID፣ ሌላ ተቋም ውስጥ ከሆነ ወይም በደንበኛው ወይም በመምሪያው የጉዳይ ሀላፊ እንዳይሰሩ ከተነገረዎት ለደንበኛው መስራት አይችሉም፣
- የ IP ውልዎት፣ የኋላ ታሪክ ምርመራዎት እና ስልጠናዎት ወቅታዊ እና ጊዜው ያላለፈበት መሆኑን ማረጋገጥ አለብዎት፣
- ማንኛውንም ያልተቋቸ ክስ፣ ወንጀለኝነት፣ ግኝት ወይም ሌላ የኋላ ታሪክ ምርመራዎች መካከል የሚፈጠር አሉታዊ እርምጃን ወዲያው ለመምሪያው ማሳወቅ አለብዎት፣
- በተመሳሳይ ወቅት ከአንድ ደንበኛ በላይ የስራ ሰአታት መጠየቅ አይችሉም
- ደንበኛን በመኪና የሚያዘዋውሩ ከሆነ በግዛቱ ህግ መሰረት ትክክለኛ/ወቅታዊ የግዛቱ የመንጃ ፈቃድ እና መድህን ሽ ሊኖርዎት ይገባል
- የእርስዎን ውል ሌላ ሰው እንዲፈጽመው ማድረግ የለብዎትም እና
- ክፍያ ለማግኘት ሁሉንም ተግባራዊ ሚደረጉ ህጎች እና ደንቦች ማክበር አለብዎት፡፡

የውሉን እና መመሪያውን ደንቦች የማያከብሩ ከሆነ ክፍያ ላይከፈልዎት እንዲሁም ውልዎት ሊቋረጥ ይችለል፡፡

# ስልጠና እና የቤት ውስጥ እንክብካቤ እርዳታ (HCA) የትምህርት መስፈርቶች

ይህ ክፍል ስለስልጠናዎት እና ማረጋገጫ መስፈርት ያብራራል፡፡ የስልጠና እና ማረጋገጫ ሂደቶችን እና ማብቃያዎችን በፍጥነት ለመረዳት የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ማረጋጫ ዝርዝርን ገጽ ላይ 15-16 ይጠቀሙ፡፡

የረዥም ጊዜ የእንክብካቤ ሰራተኞች ክፍያ ያለው የግል እንክብካቤ ከመስጠታቸው በፊት የ5 ሰአታት የመግለጫ እና ደህንነት ስልጠና እንዲያጠናቅቁ ህግ ያስገድዳል፡፡ በተጨማሪ አብዛኞቹ የረዥም ጊዜ የእንክብካቤ ሰራተኞች የ70 ሰአታት መሰረታዊ ስልጠና በተቀጠሩ በ120 ቀናት ውስጥ ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡ የ70 ሰአታት መሰረታዊ ስልጠና ማጠናቀቅ እንዳለብዎት ለማወቅ ገጽ 13-14 ላይ የሚገኘውን ሰንጠረዝ ይመልከቱ፡፡

ሁሉም ስልጠና ለግለሰብ አገልግሎት ሰጪ የሚደረገው በ SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን ነው፡፡

የግለሰብ አገልገሎት ሰጪዎች አስፈላጊውን ስልጠና በስልጠና ሽርክና በኩል ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡

## የቤት ውስጥ እንክብካቤ እርዳታ (HCA) ማረጋገጫ

ብዙ የረዥም ጊዜ የእንክብካቤ ሰራተኞች ማረጋገጫ ያላቸው የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ሰጪ መሆን አለባው፡፡ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ማግኘት ካስፈለገዎት በተቀጠሩ በ14 ቀናት ውስጥ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማመልከቻውን ለጤና መምሪያ (DOH) ማስገባት አለብዎት፡፡ ስለሚፈልጉት የስልጠና እና ማረጋገጫ መስፈርት መረጃ ለማግኘት ገጽ 13-14 ላይ የሚገኘውን የረዥም ጊዜ የእንክብካቤ ሰራተኞች የስልጠና መስፈርት ሰንጠረዥ ይመልከቱ፡፡ ሙሉ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫዎትን ለማግኘት 200 ቀናት አለዎት፡፡ የወረቀት ማመልከቻ ወይም www.doh.wa.gov/LicensesPermitsandCertificates/ProfessionsNewReneworUpdate/HomeCareAide በመጎብኘት ኦንላይን ማመልከቻ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡



ለሚያስፈልግ ስልጠና ለመመዝገብ የአባል ምንጭ ማዕከሉን እርስዎ ማነጋገር አለብዎት፡፡ የአባል ምንጭ ማዕከሉን **1-866-371-3200** ላይ በመደወል ማነጋገር ይችላሉ፡፡

የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ፈቃዱን ከጤና መምሪያው የሚወስዱ ከሆነ እና የሀሺሽ ወይም መጠጥ ችግር ታሪክ ካለዎት የጤና መምሪያው የተገደበ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ፈቃድ ይሰጥዎታል። የተገደበ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ፈቃድ ግለሰብ አገልገሎት ሰጪ ሆነው የመስራት እድልዎትን ሊያጠበው ይችላል።

*ስለ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ሂደት የበለጠ ለማወቅ :*

- *ገጽ 15-16 ላይ የሚገኘውን የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ዝርዝር ያንቡ*
- *የጤና መምሪያ ውስጥ የሚገኘው የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ አስተባበሪ ጋር በ360-236-2700 ይደውሉ*

**የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋጫ ለማግኘት ብዙ ሂደቶችን መከተል እና አስፈላጊ የጊዜ ገደቦችን ማክበር አለብዎት።** የስልጠና መስፈርቶችን እንዴት እንደሚያሟሉ ለማወቅ ገጽ 15-16 ይመልከቱ።

የተወሰነ የእንግሊዝኛ ብቃት ካለዎት (ማለትም እግሊዝኛ የማንበብ፣ መጻፍ ወይም መናገር ችሎታዎት ውስን ከሆነ) ጊዜያዊ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ከጤና መምሪያው ይሰጥዎታል። ጊዜያዊ ማረጋገጫ ሙሉ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ለማግኘት ተጨማሪ 60 ቀናት (ማለትም በአጠቃላይ 260 ቀናት) እንዲያገኙ ያደርጋል። በስራው ለመቀጠል ጊዜያዊ ማረጋገጫው የጊዜ ገደብ ከማብቃቱ በፊት ሙሉ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ሰጪ መሆን አለብዎት።

ጊዜያዊ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ለማግኘት የ DOH ማመለከቻው ላይ "እግሊዝኛ የማንበብ፣ መጻፍ ወይም መናገር ችሎታቸው ውስን ለሆነ ሰዎች የተዘጋጀ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ጊዜያዊ ማረጋገጫ" እያመለከቱ እንደሆነ የሚያሳየውን ሳጥን ምልክት ያድርጉ።

## መግለጫ እና የደህንነት ስልጠና

እንክብካቤ ከመስጠትዎት በፊት የመግለጫ እና የደህንነት ስልጠና ማጠናቀቅ አለብዎት። ውል በሚያደርጉበት ወቅት የመግለጫ እና የደህንነት ስልጠና ኦንላይን እንዴት ማጠናቀቅ እንዳለብዎት ከ DSHS ሰራተኛ መመሪያ ያገኛሉ። መግለጫ እና ደህንነት ኦንላይን የእንግሊዝኛ ትምህርት መውሰድ ካልቻሉ በርካታ አማራጮች በጥቅማ-ጥቅም ቡድኑ በኩም መሰጠት ይችላል፤ በሚከተሉት ቋንቋዎች መግለጫ እና ደህንነት መስጠትን ጨምሮ። ሩስያ፣ ቪየትናም፣ ስፔን፣ ኮርያ እና ካንቶኒስ/ቀላል ቻይንኛ።

የመግለጫ እና የደህንነት ስልጠና ኦንላይን ካጠናቀቁ በኋላ ለግለሰብ አገልገሎት ሰጪ ምድብ የሚያስፈልጉትን ትምህርቶች መመዝገብ ይችላሉ።

ስለዚህ ሂደት ጥያቄ ካለዎት የአባል ምንጭ ማዕከሉን 1-866-371-3200 ላይ ያነጋገሩ።

ስለ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ሂደት የበለጠ ለማወቅ፡

- የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ዝርዝር ያንብቡ ገጽ 15-16
- የ HCA አስተባባሪን በ DOH በ 360-236-2700 ይደውሉ።

## የ70 ሰአት ስልጠና መስፈርት

እንክብካቤ ስለሰጡ ክፍያ ከማግኘትዎ በፊት የ 5 ሰአታት የመግለጫ እና የደህንነት ስልጠና ማጠናቀቅ አለብዎት። በተጨማሪ አብዛኞቹ የረዥም ጊዜ የእንክብካቤ ሰራተኞች የ70 ሰአታት መሰረታዊ ስልጠና (አጠቃላይ ለ75 ሰአታት ስልጠና) በተቀጠሩ በ120 ቀናት ውስጥ ማጠናቀቅ አለባቸው። ሐ - በ SEIU 775 Benefits Group አማካይነት ለስልጠና ያመልክቱ

ስለ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ማመልከቻ የበለጠ ለማወቅ የ DOH ድህረ-ገጽን ይጎብኙ፡ *www.doh.wa.gov/LicensesPermitsandCertificates/ProfessionsNewReneworUpdate/HomeCareAide.aspx*

- በተቀጠሩ በ14 ቀናት ውስጥ ለስልጠና መመዝገብ አለብዎት። በአካባቢዎ ስልጠና ለማግኘት እና ለመመዝገብ SEIU 775 ጥቅማ-ጥቅም ቡድንን www.myseiubenefits.org/ ላይ ይጎብኙ ወይም የአባል ግብዐት ማዕከልን 1-866-371-3200 ላይ ይደውሉ። ለመግባት ስምዎ፣ የአባት ስም፣ የማህበራዊ ደህንነት ቁጥር መጨረሻዎቹ አራት ቁጥሮች እና ትክክለኛ የኢሜል አድራሻ ያስፈልጋል።
- የ5 ሰአት የመግለጫ እና የደህንነት ስልጠና እና የ70 ሰአታት መሰረታዊ ስልጠና ካጠናቀቁ በኋላ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ፈተና ለመውሰድ የሚያስችል የስልጠና መስፈርት (አጠቃላይ 75 ሰኣት) አሟልተዋል ማለት ነው። በኦላይን የመግለጫን የደህንነት ትህምህርትዎን በኢንግሊዝኛ ቋንቋ ኮርስ መውሰድ አልቻሉም? በጥቅማ-ጥቅም ቡድን በኩል በርካታ እድል ይሰጣል፤ በሚከተሉት ቋንቋዎች O&S መስጠትን ጨምሮ፡ ሩስያ፣ ቪየትናም፣ ስፔን፣ ኮርያ እና ካንቶኒስ/ቀላል ቻይንኛ።
- በተቀጠሩ በ14 ቀናት ውስጥ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ለማግኘት ለጤና መምሪያ ማመልከት አለብዎት። ክፍያውን ከማመልከቻዎት ጋር አያካትቱት፣ SEIU 775 የስልጠና ሽርክናው የማመልከቻ ክፍያውን በቀጥታ ለጤና መምሪያው ይከፍላል። SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን የማመልከቻ ክፍያውን እንደሚከፍለ ለማረጋገጥ ማመልከቻው ላይ 'ግዛቱ ይከፍላል' የሚለውን እባክዎ ይመልከቱ።
- በ14 ቀናት ውስት ማመልከቻዎን ካላስገቡ ወይም ለስልጠና ካልተመዘገቡ ፈተናውን አይወስዱም ወይም በጊዜ ገደቡ ብቁ አይሆኑም።
- DOH ከእርስዎ የተሟላ የ HCA ማመልከቻ ሲያገኝ እና የ75 ሰአታት ስልጠና ከጨረሱ ፈተና ለመውሰድ ዝግጁ መሆንዎን ለ ProMetric ያሳውቃል።

ስለ ቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ ፈተና እና የፈተና ማመልከቻ ሂደት የበለጠ ለማወቅ የፕሮሜትሪክ ድህረ-ገጽን ይጎብኙ፡ *https://www.prometric.com/en-us/clients/wadoh/Pages/landing.aspx*



- የመጀመሪያ ፈተና የተሰጠዎትን ግዜ ከProMetric ሮሜትሪክ ይውሰዱ።
- ፈተናውን የማለፍ ችሎታዎችን ለመጨመር ስልጠናው ወደማለቁ አካባቢ ይፈተኑ። ማስታወሻ፤ SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን ከፈተናዎ በፊት የሚወስዱት የማነቃቂያ ትምህርት ይሰጣል። የአባል ግብዐት ምዕከሉ የማነቃቂያ ትምህርት እንዲያስቀጥርልቆት እባክዎ በ1-877-371-3200 ይደውሉ። በተጨማሪ ከቡድን መሪ/አስተማሪ እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ። የቡድን መሪ/አስተማሪ ማለት ለSEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም የሚሰሩ HCA ናቸው። የቡድን መሪ/አስተማሪ በሚከተሉት ጉዳዬች ሊያግዙት ይችላል፡
  - መሰረታዊ ስልጠና ላይ ማሰልጠን ወይም ማስጠናት
  - የማረጋገጫ ሂደቱን ማሳየት
  - በስልጠና የተማርነውን ችሎታ በስራ ላይ ወደ እውነታ መተግበር
  - ለሙያዊ እድገት እድሎችን እና ተጨማሪ ስልጠና ውይይት ምንጭ መሆን
  - አጠቃላይ ድጋፍ ወይም ማበረታታት መስጠት
  - እርስዎን ለድጋሚ ፈተና ለማዘጋጀት ተጨማሪ ችሎታ እና የእውቀት ድጋፍ መስጠት
    - ይጎብኙ: www.myseiubenefits.org/peermentors/
    - ወይም ለቡድን መሪ/አስተማሪ 1-855-803-2095 ላይ ይደውሉ
    - ወይም ለቡድን መሪ/አስተማሪ Peer.Mentorship@myseiubenefits.orgላይ ኢሜል ያድርጉ
- ስለማረጋገጫ ፈተናው አስፈላጊ መረጃ በኢሜል ይደርስዎታል። የፈተና ቀንዎትን ለማረጋገጥ ከ DOH ለሚላክልዎት የፈተና ኢሜል ማረጋገጫ መመለስ አለብዎት። ማመልከቻዎትን ካስገቡ በኋላ ፈተናውን በተመለከተ ኢሜል ተልኮ እንደሆነ ለማረጋጥ በመደበኛነት የኢሜል ኢንቦክስ፣ ጀንክ እና ስፓም መሀደሮችን ይመልቱ። ማመልከቻዎት ላይ የኢሜል አድራሻ ካልጻፉ ፕሮሜትሪክ የማረጋጫ ፈተናውን ቀጠሮ አያስይዝም።

## ከ70 ሰአት ስልጠና እና የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ (HCA) ማረጋጫ ነጻ ስለመደረግ

ነጻ ከተደረጉ የ70 ሰአት ስልጠና ወይም የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ሰጪ ማረጋገጫ አያስፈልግዎትም። ሊተዉ የሚችሉበት ምክንያቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ ግን በዚህ አያበቃም፡

- ከጤና መምሪያ ጥሩ ውጤት ያለው የሚሰራ ማስረጃ ያለው የተመዘገበ ነርስ (RN)፣ ፈቃድ ያለው በስራ ላይ ያለ ነርስ (LPN)፣ ከፍተኛ የተመዘገበ በስራ ላይ ያለ ነርስ (ARNP) ወይም ማረጋገጫ ያለው ረዳት-ነርስ (NAC) ከሆነ።
- በልዩ ትምህርት ከህዝብ ትምህርት ዋና ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት (OSPI) የተሰጠ ጥሩ ውጤት ያለው የማስተማር ማረጋገጫ ካለው።
- በ1/1/2011 እና 1/6/2012 መካከል በ Washington ግዛት የረዥም ጊዜ እንክብካቤ ስርአት ውስጥ የሰራ እና በዛ ሰአት ሁሉንም የስልጠና መስፈርት ያሟላ።

  *የረዥም ጊዜ እንክብካቤ ስርአት ምሳሌ፡ በግዛቱ የሚተዳደር ድጋፍ ያለበት የመኖሪያ ቦታ ውስጥ ሚገኙ (ማደሪያ ቤቶች)፣ አዋቂዎ ሰዎች የቤተሰብ ቤት፣ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ኤጀንሲ ውስጥ ለሚኖሩ ለአረጋውያን ወይም አካል ጉዳተኛ ሰዎች ክፍያ ያለው፣ የግል እንክብካቤ አገልግሎት መስጠት ወይም ለ DSHS ደንበኛ የግለሰብ አገልገሎት መስጠት።*

## ለወላጅዎ ወይም ለልጅዎ አገልገሎት የሚሰጡ ከሆነ

ለወላጅዎ ወይም ለልጅዎ ብቻ የረዥም ጊዜ እንክብካቤ አገልገሎት የሚሰጡ ከሆነ ለአዋቂ ልጅ፣ ለወላጅ ወይም የወላጅ DD አገልግሎት ሰጪ ነዎት ማለት ነው። አዋቂ ልጅ እና ወላጅ አገልግሎት ሰጪ የ70 ሰኣት ስልጠና ማጠናቀቅ የለባቸውም። የእርስዎን የግለሰብ አገልገሎት ሰጪ ምድብ የስልጠና መስፈርት ለማየት ገጽ 13-14 ላይ የሚገኘውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

የእርስዎ ወላጅ ወይም ልጅ ያልሆነ ደንበኛ ካለዎት የስልጠና መስፈርቶችዎት ይቀየራሉ። አሁን ያለዎትን የስልጠና መስፈርት ለመረዳት እርዳታ ካስፈለገዎት የአባል ምንጭ ማዕከሉን 1-866-371-3200 ላይ ይደውሉ።

## እንክብካቤ የሚሰጡት ለአንድ ሰው ከሆነ፣ በወር 20 ሰአት ወይም ከዛ በታች

በወር ለአንድ ሰው ብቻ ከ20 ሰኣት ያነሰ እንክብካቤ የሚሰጡ ከሆነ የተገደቡ አገልገሎት ሰጪ ነዎት ማለት ነው። የተገደቡ አገልገሎት ሰጪዎች የ70 ሰአት መሰረታዊ ስልጠና ማጠናቀቅ አለባው። የተገደቡ አገልገሎት ሰጪዎች የስልጠና መስፈርት ለማየት ገጽ 13-14 ላይ የሚገኘውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

ሌላ ደንበኛ ከወሰዱ ወይም የሚሰሩበትን ሰአት ከጨመሩ የስልጠና መስፈርትዎ ይቀየራል። አሁን ያለዎትን የስልጠና መስፈርት ለመረዳት እርዳታ ካስፈለገዎት የአባል ምንጭ ማዕከሉን 1-866-371-3200 ላይ ይደውሉ።

### የእረፍት ጊዜ ብቻ አገልግሎት ሰጪ

የእረፍት ጊዜ እንክብካቤ ብቻ ማለትም በየአመቱ ከ300 ሰኣት በታች ለደንበኛ የሚሰጡ ከሆነ የ70 ሰኣት መሰረታዊ ስልጠና ማጠናቀቅ የለብዎትም። የእረፍት ጊዜ ብቻ እንክብካቤ ሰጪዎች ስልጠና መስፈርትን ለማየት ገጽ 13-14 ላይ የሚገኘውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ። በአመት ውስጥ ከ300 ሰኣት በላይ የእረፍት ጊዜ እንክብካቤ ከሰጡ ስለጠና መውሰድ እና የ70 ሰኣት መሰረታዊ ስልጠና እንዲሁም ማረጋጫ መስፈርት ማሟላት አለብዎት። ይህ የሚሆነው ወደፊት ከሚሰጡት የእረፍት ጊዜ እንክብካቤ ሰአት ቁጥር ባሻገር ነው።

የ70 ሰአታት መሰረታዊ ስልጠና ከመውሰድ ቢተዉ እና ትምህር እንዲቀጥሉ ቢደረግም ብዙ እንክብካቤ ሰጪዎች ተጨማሪ ስልጠና መውሰድ ይፈልጋሉ። ለእርስዎ የሚገኝ የስልጠና እድል ለማወቅ እባክዎ የአባል ግብአት ማዕከል 1-877-371-3200 ላይ ያነጋግሩ።

## አስፈላጊ የስልጠና እና/ወይም የማረጋገጫ የጊዜ ገደቦችን አለማሟላት

በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የስልጠና እና ማረጋጫ መስፈርቶችን ካላሟሉ ክፍያ ይቋረጣል፡፡ እንዚህ የጊዜ ገደቦች አይራዘሙም፡፡ መምሪያው ስራ እንዲያቆሙ የሚገልጽ ማስታወቂያ ይልክ እና ክፍያዎትን ለማቆም እርምጃ ይወስዳል፡፡

የግለሰብ አገልገሎት ሰጪ ሆነው ወደስራ ለመመለስ ወይም ድጋሚ ክፍያ ለማግኘት በእርስዎ ግለሰብ አገልገሎት ሰጪ ምድን ስር የለውን ሁሉንም የስልጠና እና ማረጋጫ መስፈርቶች በራስዎት መንገድ እና በራስዎት ወጪ ማሟላት አለብዎት፡፡

## ወደስራ መመለስ

የስልጠና የጊዜ ገደብ ካለፈብዎት ቀሪውን አስፈላጊ ስልጠና በማህበረሰብ አስተማሪ አማካኝነት እራስዎት ከፍለው ማጠናቀቅ አለብዎት፡፡ የጊዜ ገደብ ካለፈ SEIU 775 ጥቅማ-ጥቅም ቡድን እያንዳንዱን ጉዳይ እያየ ስልጠና ሊሰጥ ይችላል፡፡ SEIU 775 ጥቅማ-ጥቅም ቡድን የፈቃድ ሂደት ያካሁዳል፡፡ የስልጠና የጊዜ ገደብ ካለፈብዎት በእርስዎ እና SEIU 775 ስልጠና ሽርክና መካከል DSHS ጣልቃ አይገባም፡፡ ብዙጊዜ የስልጠና ጊዜ ገደብዎን ካለፉ የማረጋገጫ የጊዜ ገደብዎትንም ያልፋሉ፡፡ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የአባል ምንጭ ማዕከሉን 1-866-371-3200 ላይ ያነጋግሩ፡፡

የማህበረሰብ አስተማሪዎች ዝርዝር ለማግኘት የDSHS አረጋውያን እና የረዝም ጊዜ እርዳታ አስተዳደር ድህረ-ገጽን www.dshs.wa.gov/altsa/home-and-community-services/individual-providers ይመልከቱ እና "የማህበረሰብ አስተማሪ ፈልግ" የሚለውን ይጫኑ፡፡

የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ የጊዜ ገደብ ካለፈብዎት በጤና መምሪያው እና ፕሮሜትሪክ በኩል የሚገለጸውን ማንኛውንም እርምጃ መውሰድ እና የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ማረጋገጫ መግኘት አለብዎት፡፡

የቀጣሪዎትን የጉዳይ ሀላፊ ያነጋግሩ እና የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ሆነው ወደስራ እንዲመለሱ ይጠይቁ፡፡ ከ SEUI 775 ስልጠና ሽርክናው ውጪ ለወሰዱት ትምህርቶች የስልጠና ማረጋጫ ቅጂ እና ማረጋጫ እንዳገኙ የሚያሳይ ሰነድ ለጉዳይ ሀላፊው ማሳየት አለብዎት፡፡

## የነርስ ተልዕኮ መስፈርቶች

ማንኛውም የነርስ ስራ (የኢንሱሊን መርፌ መውጋትን ጨምሮ) በነርስ ተልዕኮ በኩል የሚሰጥዎት (የሚላክልዎት) ከሆነ ተጨማሪ የስልጠና እና ማረጋጋጫ መስፈርት አለዎት።

የተልዕኮ ስራዎችን ለመስራት ከሚከተሉት አንዱ ማረጋገጫ ሊኖርዎት ይገባል:

- ረዳት ነርስ- የተመዘገበ (NAR)
- ረዳት ነርስ- የተረጋገጠ (NAC)
- የተረጋገጠ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ (HCA)

  እና

የሚከተሉትን መስፈርቶች ማጠናቀቅ አለብዎት:

- የነርስ ረዳት CORE የነርስ ተልዕኮ።
- የነርስ ረዳት የነርስ ተልዕኮ። በስኳር ህመም ላይ ልዩ ትኩረት (የኢንሱሊን መርፌ የሚወጉ ከሆነ)

## ቀጣይ የትምህርት መስፈርት

አብዛኞቹ የረዥም ጊዜ እንክብካቤ ሰራተኞች በየአመቱ ከልደት ቀናቸው በፊት የ12 ሰአት ቀጣት ትምህርት (CE) ማጠናቀቅ አለባቸው። የእርስዎን ሁኔታ የሚመለከት መስፈርት ዝርዝር ለማወቅ ገጽ 13-14 ላይ የሚገኘውን የረዥም ጊዜ እንክብካቤ ሰራተኞች የስልጠና መስፈርቶች ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

ቀጣይነት ያላቸው ትምህረቶችን በእንግሊዝኛ እና በሌላ ቋንቋ ለማግኘት:

- SEIU 775 ጥቅማ-ጥቅም ቡድን በሚከተለው ይጎብኙ: www.myseiubenefits.org/
- የአባል ምንጭ ማዕከል ጋር ይደውሉ: 1-866-371-3200
- የረዥም-ጊዜ እንክብካቤ ሰራተኛ ስልጠና መረጃ ከፈለጉ የ DSHS አረጋውያን እና የረዥም ጊዜ እርዳታ አስተዳደር ድህረ-ገጽ ይጎብኙ https://fortress.wa.gov/dshs/adsaapps/Professional/training/training.aspx

## ግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ምድቦች እና የስልጠና መስፈርቶች፣ ጁን 2017

| ግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ምድብ | መግለጫ እና ደህንነት | | መሰረታዊ ስልጠና | | | | HCA ማስረጃዎች | የመጀመሪያ ቀጣይ ትምህርት (CE) | በሂደት ላይ ያለ ቀጣይ ትምህርት(CE) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መግለጫ 2 ሰአታት | የደህንነት ስልጠና 3 ሰአታት | መሰረታዊ ስልጠና 9 ሰአታት | መሰረታዊ ስልጠና 30 ሰአታት | መሰረታዊ ስልጠና 70 ሰአታት | የወላጅ አገልግሎት ሰጪ ትምህርት 7 ሰአታት (DDA ብቻ) | HCA ማስረጃዎች መሞላት ያለበት:- | ቀጣይ ትምህርት (CE) 12 ሰአታት | ቀጣይ ትምህርት (CE) 12 ሰአታት |
| **መደበኛ አገልግሎት ሰጪ፣ ምድብ 1**<br>ከ1/6/2012 በኋላ ያለምንም ማስረጃ የተቀጠረ፡፡ | እንክብካቤ ከመስጠት በፊት ስልጠና ያጠናቀቀ | እንክብካቤ ከመስጠት በፊት ስልጠና ያጠናቀቀ | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | አገልግሎት ለመስጠት በተጀመረ በ120 ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡ | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | አዎ፣ በተቀጠሩ በ200 ቀናት ውስጥ፡፡ | በልደት ቀንዎት ወይም ከአንድ ቀን በፊት የ HCA ማስረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተሰጥዎት ቀን በአመቱ፡፡ | በየአመቱ በልደት ቀንዎት ወይም ከአንድ ቀን በፊት |
| **መደበኛ አገልግሎት ሰጪ፣ ምድብ 2፡**<br>ከ1/6/2012 በኋላ በ HCA ማስረጃ የተቀጠረ፡፡ | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም :- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | አዎ፣ ማስረጃዎትን መያዝ አለብዎት፡፡ | የመጀመሪያው ማስረጃዎት ማገልገል ከሚጀምርበት ቀን አንድ አመት በኋላ በልደት ቀንዎ ቀን ወይም ከዛ በፊት፡፡ | በየአመቱ በልደት ቀንዎት ወይም ከአንድ ቀን በፊት |
| **ነጻ የተደረገ መደበኛ አገልግሎት ሰጪ፣ ምድብ 1፡**<br>በ1/1/2011 እና 1/6/2012 መካከል የረዥም ጊዜ የእንክብካቤ ሁኔታ ውስጥ የሰራ እና በዛ ሰአት መሰረታዊ የስልጠና መስፈርቶችን ያሟላ፡፡<br><br>የረዥም ጊዜ የእንክብካቤ ስራዎች ምሳሌ የግል የእንክብካቤ አገልግሎቶች መንግስት ፈቃድ በተሰጠው የመኖሪያ ድጋፍ ቦታዎች፣ የአረጋውያን መኖሪያ ቤት፣ የመንከባከቢያ ቤት ኤጀንሲዎች ለሚገኙ ለአረጋውያን ወይም ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች በክፍያ መስጠትን ወይም ለ DSHS ደንበኛ ግለሰብ አገልግሎት ሰጪን ያካትታል፡፡ | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም :- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | አይ | በልደት ቀንዎት ቀን ወይም ከዛ በፊት በስራ ላይ እያሉ ወይም ወደ ስራ ሲመለሱ፡፡ | በየአመቱ በልደት ቀንዎት ወይም ከአንድ ቀን በፊት<br><br>የረዥም ጊዜ እንክብካቤ ለሰሩበት ለእያንዳንዱ አመት CE ማጠናቀቅ አለብዎት |
| **ነጻ የተደረገ መደበኛ አገልግሎት ሰጪ፣ ምድብ 2፡**<br>የሚሰራ የ WA ግዛት የተመዘገበ/ች ነርስ፣ ከፍተኛ የተመዘገበ/ች ነርስ፣ ፈቃድ ያለው/ላት የሚተገብር ነርስ ወይም የነርስ ቴክኒሺያን ማስረጃ ያላቸው፡፡ | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም :- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | አይ፣ የ APRN፣ RN ወይም LPN ማስረጃ በጥሩ ሁኔታ እስከተያዘ ድረስ፡፡ | የ APRN፣ RN ወይም LPN ማስረጃዎትን በጥሩ ሁኔታ ይያዙ፡፡ | የ APRN፣ RN ወይም LPN ማስረጃዎትን በጥሩ ሁኔታ ይያዙ፡፡ |
| **ነጻ የተደረገ መደበኛ አገልግሎት ሰጪ፣ ምድብ 3፡**<br>የሚሰራ የ WA ግዛት ረዳት ነርስ፣ የምስክር ወረቀት ማስረጃ ያላቸው፡፡ | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም :- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | አይ፣ የ NACማስረጃ በጥሩ ሁኔታ እስከተያዘ ድረስ፡፡ | የመጀመሪያውን ሰርተፊኬት ካገኙበት ቀን ከአንድ ሙሉ አመት በኋላ በልደት ቀንዎት ወይም ከዛ በፊት፡፡ | በየአመቱ በልደት ቀንዎት ወይም ከአንድ ቀን በፊት የረዥም ጊዜ እንክብካቤ ለሰሩበት ለእያንዳንዱ አመት CE ማጠናቀቅ አለብዎት |
| **ነጻ የተደረገ መደበኛ አገልግሎት ሰጪ፣ ምድብ 4፡**<br>ከህዝብ መመሪያ ቁጥጥር ጽ/ቤት (OSPI) ልዩ የትምህርት ድጋፍ ያለው | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም :- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | መሙላት ግዴታ አይደለም:- | አይ፣ የልዩ ትምህርት ድጋፍ በጥሩ ሁኔታ እስከተያዘ ድረስ፡፡ | የመጀመሪያውን ሰርተፊኬት ካገኙበት ቀን ከአንድ ሙሉ አመት በኋላ በልደት ቀንዎት ወይም ከዛ በፊት፡፡ | በየአመቱ በልደት ቀንዎት ወይም ከአንድ ቀን በፊት የረዥም ጊዜ እንክብካቤ ለሰሩበት ለእያንዳንዱ አመት CE ማጠናቀቅ አለብዎት |

## ግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ምድቦች እና የስልጠና መስፈርቶች፣ ጁን 2017

| ግለሰብ አገልግሎት ሰጪ/ በኤጀንሲ የተቀጠረ አገልግሎት ሰጪ ክፍፍል | መግለጫ እና ደህንነት | | መሰረታዊ ስልጠና | | | | ማስረጃዎች | የመጀመሪያ ቀጣይ ትምህርት (CE) | በሂደት ላይ ያለ ቀጣይ ትምህርት(CE) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መግለጫ 2 ሰአታት | የደህንነት ስልጠና 3 ሰአታት | መሰረታዊ ስልጠና 9 ሰአታት | መሰረታዊ ስልጠና 30 ሰአታት | መሰረታዊ ስልጠና 70 ሰአታት | የወላጅ አገልግሎት ሰጪ ትምህርት 7 ሰአታት (DDA ብቻ) | HCA ማስረጃዎች መሞላት ያለበት፡- | ቀጣይ ትምህርት (CE) 12 ሰአታት | ቀጣይ ትምህርት (CE) 12 ሰአታት |
| *** ወላጅ አገልግሎት ሰጪ**<br>ለእራሱ/ሷ ልጅ፣ እንጀራ ልጅ ወይም ማደጎ ልጅ የግል እንክብካቤ የሚሰጥ | እንክብካቤ ከመስጠት በፊት ስልጠና ያጠናቀቀ | እንክብካቤ ከመስጠት በፊት ስልጠና ያጠናቀቀ | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | አገልግሎት ለመስጠት በተጀመረ በ120 ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡ | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | አይ | የ HCA ማስረጃዎትን በፈቃደኝነት ካላገኙ በስተቀር መሙላት ግዴታ አይደለም | የ HCA ማስረጃዎትን በፈቃደኝነት ካላገኙ በስተቀር መሙላት ግዴታ አይደለም |
| *** ወላጅ የ DD አገልግሎት ሰጪ፡**<br>ለእራሱ/ሷ አካል ጉዳተኛ ልጅ፣ እንጀራ ልጅ ወይም ማደጎ ልጅ የግል እንክብካቤ የሚሰጥ | እንክብካቤ ከመስጠት በፊት ስልጠና ያጠናቀቀ | እንክብካቤ ከመስጠት በፊት ስልጠና ያጠናቀቀ | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | አገልግሎት ለመስጠት በተጀመረ በ120 ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡ | አይ | የ HCA ማስረጃዎትን በፈቃደኝነት ካላገኙ በስተቀር መሙላት ግዴታ አይደለም | የ HCA ማስረጃዎትን በፈቃደኝነት ካላገኙ በስተቀር መሙላት ግዴታ አይደለም |
| *** የተወሰነ አገልግሎት ሰጪ፡**<br>ለአንድ ሰው በወር የ20 ሰአታት (ወይም ከዛ ያነሰ) እንክንካቤ ይሰጣል | እንክብካቤ ከመስጠት በፊት ስልጠና ያጠናቀቀ | እንክብካቤ ከመስጠት በፊት ስልጠና ያጠናቀቀ | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | አገልግሎት ለመስጠት በተጀመረ በ120 ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡ | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | አይ | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- |
| *** ለአቅመ-አዳም የደረሰ ልጅ አገልግሎት ሰጪ፡**<br>ለአቅመ-አዳም የደረሰ ልጅ ለእራሱ/ሷ አካል ጉዳተኛ ወላጅ፣ እንጀራ ወላጅ ወይም ማደጎ ወላጅ የግል እንክብካቤ የሚሰጥ | እንክብካቤ ከመስጠት በፊት ስልጠና ያጠናቀቀ | እንክብካቤ ከመስጠት በፊት ስልጠና ያጠናቀቀ | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | አገልግሎት ለመስጠት በተጀመረ በ120 ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡ | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | አይ | መሰረታዊ ስልጠና ከተጠናቀቀ በኋላ፣ በልደት ቀንዎት ወይም ከዛ በፊት በሚቀጥለው በሚቀጥለው አመት | በየአመቱ በልደት ቀንዎት ወይም ከአንድ ቀን በፊት |
| ****የእረፍት ጊዜ ብቻ እንክብካቤ ሰጪ**<br>በ DDA የእረፍት ጊዜ ብቻ እንክብካቤ ሰጪ ለግለሰብ እንክብካቤ መስጠት፣ በየትኛውም አመት ከ300 ሰአት በታች መስራት | እንክብካቤ ከመስጠት በፊት ስልጠና ያጠናቀቀ | እንክብካቤ ከመስጠት በፊት ስልጠና ያጠናቀቀ | አገልግሎት ለመስጠት በተጀመረ በ120 ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡ | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | ***አይ | ****መሙላት ግዴታ አይደለም፡- | መሙላት ግዴታ አይደለም፡- |

* አገልግሎት የሚሰጡትን ደንበኛ አይነት እና ቁጥር ከቀየሩ ወይም የሚሰሩትን ሰአት ከጨመሩ የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ምድብዎት ሊቀየር ይችላል፡፡ ይህ የስልጠና እና ማረጋገጫ መስፈርትዎን ሊጨምር ይችላል፡፡

** የ DDA የእረፍት ጊዜ እንክብካቤ ሰጪ በአንድ አመት ውስጥ ከ300 ሰአት በላይ ከሰራ ወደመደበኛው የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ምድብ በቋሚነት ይመለሳል፡፡

*** የ DDA የእረፍት ጊዜ እንክብካቤ IP የ300 ሰአት ገደቡን ካለፈ ጊዜው ያለፈበት የ HCA ማስረጃ ለማደስ 30 ቀን ይኖረዋል፡፡

**** የ DDA የእረፍት ጊዜ እንክብካቤ IP የ300 ሰአት ገደቡን ካለፈ እና ነጻ የተደረገ IP መስፈርት ካሟላ የ CE መስፈርት ማጠናቀቅ አለበት፡፡

Washington State Department of Social & Health Services
Transforming lives

# ወደ የሰዎች ማዕከል ቤት በሰላም መጡ እንደ ግለሰብ እንክብካቤ አቅራቢ

**Welcome to Person Centered Home Care as an Individual Provider**

**የህግ መስፈርቶች:**

በተቀጠሩ (ስልጣን ተሰጥቶዎት አገልግሎት ከተጀመረበት ቀን) በ**120** ቀናት ውስጥ (የ 5 ሰዓታት መግለጫና ደህንነትን ጨምሮ) የ **75** ሰዓታት ልምምድ መፈጸም ግዴታ ያለበዎት ሲሆን ከዚያ ቦኋላ በተቀጠሩ በ**200** ቀናት ውስጥ የተረጋገጠለት የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት ይሆናሉ:: እነዚህን ሊፈጸምበት የተቀመጡ የግዜ ገደባትን ሚሟላት ካልቻሉ እየተከፈለዎት መቀጠል አይችሉም:: የተቀመጠውን የግዜ ገደብ ለመተግበር የግዜ ወሰኑንና ማመሳከሪያ መስፈርቶቹን ይጠቀሙ::

## ሀ - ስለመጀመር

| | **እርምጃ:-** | **ማስታወሻዎች** | ✓ |
|---|---|---|---|
| ቅደም ተከተል 1: | ውል ከማድረግዎ በፊት የኦንላይን WA ግዛት የኋላ ታሪክ ምርመራ ፈቃድ ቅጽ መሙላት አለብዎት:: ካልሆነ ውል የሚያደርጉትን ጽ/ቤት ያነጋግሩ:: | የኋላ ታሪክ ምርመራ ውጤትዎን ቅጂ ያስቀምጡ! ስለኋላ ታሪክ ምርመራ የበለጠ መረጃ ለማግኘት BCCU Website ይጎብኙ:: | ☐ |
| ቅደም ተከተል 2: | የWA ግዛት የኋላ ታሪክ ምርመራ ካለፉ ውል የሚያደርጉት ጽ/ቤት **የጣት አሻራ ቀጠሮ ቅጽ መጠየቂያ ID# ወይም OCA#** ከሚባል መለያ ቁጥር ጋር ይሰጥዎታል:: **መጠየቂያ ID#/OCA#** እዚህ ይጻፉ:______________ | የእርስዎ መጠየቂያ ID#/OCA# ለጣት አሻራ ቀጠሮዎት እና ለጤና መምሪያ (DOH) ማመልከቻዎት ያስፈልጋል:: | ☐ |
| ቅደም ተከተል 3: | የመጠየቂያ ID#/OCA# ከጣት አሻራ ቀጠሮዎት ጋር ካገኙ በቅርብ በሚገኘው የጣት አሻራ መስጫ **የጣት አሻራ ወዲያው ያስወስዱ::** ቀጠሮ ለማስያዝ የጣት አሻራ መስጫ ቦታ ይጎብኙ:: የቀጠሮ ሰአት እና ቦታ እዚህ ይጻፉ: ____________________ | አጀንዳዎት ላይ ምልክት ያድርጉ እና ቀጠሮው ላይ የጣት አሻራ ቀጠሮ ቅጽ እና ፎቶ ያለበት መታወቂያ ይዘው ይምጡ! **ጣት አሻራ ውጤትዎ በ120 ቀናት ውስጥ ካልተሰጥዎት መስራት አይችሉም::** | ☐ |
| ቅደም ተከተል 4: | **እንክብካቤ ከመስጠትዎ በፊት:** የመግለጫ እና የደህንነት የስልጠና ትህምህርትዎን **ኦንላይን በእንግሊዝኛ** SEIU 775 Benefits Group ላይ ይውሰዱ::<br><br>ለመግባት ስምዎ፣ የአባት ስም፣ የማህበራዊ ደህንነት ቁጥር መጨረሻዎቹ አራት ቁጥሮች እና ትክክለኛ የኢሜል አድራሻ ያስፈልጋል:: | በኦላይን የመግለጫን የደህንነት ትህምህርትዎን በኢንግሊዝኛ ቋንቋ ኮርስ መውሰድ አልቻሉም? በኮንትራት ቀጠሮዎት ወቅት የተለያዩ አማራጮች ሊቀርብልዎት ይችላል:: ይህ በሚከተሉት ቋንቋዎች መግለጫ እና ደህንነት መስጠትን ያካትታል: ሩስያ፣ ቪየትናም፣ ስፔን፣ ኮርያ እና ቀላል ቻይንኛ:: | ☐ |

## ለ - የ DOHን ማመልከቻ ይሙሉ እና ያስገቡ

| | **እርምጃ:-** | **ማስታወሻዎች** | ✓ |
|---|---|---|---|
| ቅደም ተከተል 1: | ✷ **በተቀጠሩ በ14 ቀናት ውስጥ እንዲተገብሩት የሚመከር:- የጤና ክፍል (DOH)** ኤችሲኤ ማመልከቻ. ስለፈተናዎ እና የ DOH የምስክር ወረቀትዎ እንዲሁም ፕሮሜትሪክ ለመነጋገር ቢያንስ አንድ የኢሜል አድራሻ መስጠት አለብዎት:: የ DOH ማመልከቻዎን ካስገቡ እና መሰረታዊ የ70 ሰአታት ስልጠና ካሟሉ በኋላ የ HCA ፈተና ቀን ይነገርዎታል:: ክፍያ አይከፍሉም፤ እባክዎ **ማመልከቻው ላይ 'መንግስት የሚከፍል' ምልክት ያድርጉ** እና ክፍያ በ SEIU 775 Benefits Group ይከፈላል:: | **ማመልከቻዎን በ14 ቀናት ውስት ካላስገቡ ፈተናውን አይወስዱም ወይም በጊዜ ገደቡ ብቁ አይሆኑም::**<br><br>DOH ማመልከቻዎን ካገኘው ባለ10 አሀዝ የ DOH ማረጋገጫ # (HM) ይሰጥዎታል::<br><br>በ (360) 236-2700 ላይ የ HCA መረጃ አስተባባሪን ሲያገኙ ወይም ከ DOH በቀጥታ የመረጃ መረብ መረጃ ሲያገኙ ይህንን ቁጥር ይጠቀሙ:: | ☐ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቅደም ተከተል 2፡ | ውስን የእንግሊዝኛ ብቃት (LEP) ካለዎት ማለትም እንግሊዝኛ የማንበብ፣ መጻፍ ወይም ማናገር ችሎታዎት ውስን ከሆነ ለተጨማሪ የ60 ቀናት ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ብቁ የሚሆኑበትን የጊዜ ገደብ ማራዘም የስልጠና የጊዜ ገደብን እንደማያራዝም እባክዎ ይወቁ፡፡ | LEP ብቻ፡ ጊዜያዊ የምስክር ወረቀቱን እንደሚፈልጉት በ DOH ማመልከቻዎት ላይ ምልክት ያድርጉ፡፡ | ☐ |
| ቅደም ተከተል 3፡ | በእስፓኒሽ፣ በራሽይኛ፣ ቬትናም፣ ኮሪያ ቻይንኛ፣ ካምቦድያ፣ ሉኣቲንያ፣ ሳሞኣን፣ ሱማሊኛ፣ ዩክሬን፣ ታጋሎግ፣ አማሪኛ፣ ወይንመ በአረብኛ የ HCA ፈተና ለመውሰድ በ HCA ፈተና ማመልከቻ ላይ የቋንቋ ፈላጎትዎን ያረጋግጡ፡፡<br><br>ከተገለጸው ውጪ በሆነ ቋንቋ ፈተናውን መውሰድ ከፈለጉ በፕሮሜትሪክ ድህረ-ገጹ ላይ የሚገኘውን ለፈተና የሚያስፈልጉ ነገሮች ጥያቄ አሽግ በመሙላት እና በዚህ ቅጽ ላይ ለሚገኘው አድራሻ በማስገባት የራስዎን ቋንቋ የግል አስተርጓሚ መጠየቅ ይችላሉ፡፡<br><br>እባክዎ መረጃውን እዚህ ያኙሉ: [የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋፍ ፈተና መኖሪያ መጠየቂያ አሽግ] | ለአስተርጓሚ/ለሚያስፈልጉ ነገሮች ጥያቄ 30 ቀናት ሊወስድ ይችላል፡፡<br><br>**DOH ኢ-ሜል ይልካል፡፡ ለማረጋገጥ ምላሽ መስጠት አለብዎት፡፡ ለኢ-ሜሉ ምላሽ ካልሰጡ ማመልከቻዎ ያልተሟላ ይሆናል፡፡**<br><br>ስልጠናዎትን ካጠናቀቁ በኋላ ከ DOH እና ፕሮሜትሪክ ኢ-ሜል መምጣቱን ለማየት የኢ-ሜል ኢንቦክስ፣ ጀንክ እና ስፓም መሀደሮችን በየእለቱ ይመልከቱ! | ☐ |

## ሐ - በ SEIU 775 Benefits Group አማካይነት ለስልጠና ያመልክቱ

| | እርምጃ፡- | ማስታወሻዎች | ✓ |
|---|---|---|---|
| ቅደም ተከተል 1፡ | ✷ **በተቀጠሩ በ14 ቀናት ውስጥ እንዲተገብሩት የሚመከር፡-** ለ70 ሰአታት መሰረታዎ ስልጠና በ NW የስልጠና ጥምረት (TP) ድህረገጽ አማካኝነት https://www.myseiubenefits.org/ ላይ ይመዝገቡ፡፡ | እንትርኔት ለመጠቀም አላቻሉም? አባል የግብአት ማዕከል ጋር በሚከተለው ይደውሉ፡ 1-866-371-3200 | ☐ |
| ቅደም ተከተል 2፡ | ✷ **በተቀጠሩ በ60 ቀናት ውስጥ እንዲተገብሩት የሚመከር፡** በሚኖሩበት አካባቢ ትምህርት እንዲያገኙ እና የተፈና እና የምስክር ወረቀት የጊዜ ገደቦችን አሚልተው በወቅቱ ትምህረት እንዲያገኙ የ70 ሰአታት መሰረታዊ ስልጠናዎትን ቶሎ ያጠናቁ፡፡ | የ75 ሰአታት ስልጠና ከተጠናቀቀ በኋላ በ My Benefits portal የማጠናቀቅ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይችላሉ፡፡ በመቀጠል SEIU 775 Benefits Group በእርስዎ ስም ለጤና መምሪያው (DOH) ያስተላልፈዋል፡፡ | ☐ |
| ቅደም ተከተል 3፡ | እዚህ የስልጠናውን ቀንና ቦታ ይፃፉ፡--------------------- | የቀን መቁጠሪያዎትን ምልክት ያድርጉ! | ☐ |

## መ -በፕሮሜትሪክ አማካኝነት የሚመረመር

| | እርምጃ፡- | ማስታወሻዎች | ✓ |
|---|---|---|---|
| ቅደም ተከተል 1፡ | የእውቀት እና ችሎታ የጽሁፍ ፈተናውን ይለፉ፡ የፈተናውን ቀንና ቦታ እዚህ ይፃፉ፡ ____________________________<br><br>**የመጀመሪያ ፈተና የተሰጠዎትን ግዜ ከፕሮሜትሪክ ይውሰዱ፡፡**<br>ፈተናውን የማለፍ ችሎታዎትን ለመጨመር ስልጠናው ወደማለቁ አካባቢ ይፈተኑ፡፡<br><br>ጉዳዩ በሚለው መስመር ላይ የፈተና መረጃ፣ ስምዎትን፣ የፕሮሜትሪክ የመታወቂያ # የያዘ ኢ-ሜል ከ **Pbt-admit@Prometric.com** ይጠብቁ (የኢንቦክስ፣ ጀንክ እና ስፓም መሀደሮችን ይመልከቱ)፡፡ | **ፕሮሜትሪክ መልዕክት የሚልክልዎት በ DOH ማመልከቻዎት ላይ በሰጡት አሜል አድራሻ ብቻ ነው፡፡**<br>ስልጠና ባጠናቀቁ በ14-28 ቀናት ውስጥ ከፕሮሜትሪክ በኢ-ሜል የተገለጸ የፈተና ቀን ካላገኙ ፕሮሜትሪክን በ1-800-324-4689 ያነጋግሩ፡፡<br>ስልጠና ላይ ክለሳ ወይም ድጋፍ ካስፈለገዎት እባክዎ MRCንን ያነጋግሩ ወይም የሚከተለውን ይጎብኙ [SEIU 775 DOH Steps to Get Certified] | ☐ |
| ቅደም ተከተል 2፡ | ሙከራውን ከወደቁ ወዲያውኑ ለፈተና ያስቀጥሩ፡፡ በድጋሚ ፈተና ለመፈተን ወዲያው ፕሮሜትሪክን ያነጋግሩ፡፡<br><br>የወደቁትን ፈተና ድርሻ ሁለት ግዜ ይውሰዱ፡፡<br>ለያንዳንዱ ዳግም መፈተኛ ክፊያ መክፈል ይጠበቅብዎታል፡፡ | ሰለማረጋገጫዎት # መረጃ<br>የ DOH ድህረገጽ ላይ ይገኛል: [የአገልግሎት ሰጪ ማረጋገጫ ፍለጋ] (HM ወይም PV).<br>እውቅናዎት ፈጣን (““Active”)ካመለከተ፤ መስራት ይችላሉ፡፡ በጤና ክፍል ድረ-ገፅ ፈጣን ሳይሆኑ ከ200 ቀናት እላፊ መስራት አይችሉም፡፡ | ☐ |

| ኤጀንሲ | ስልክና ፋክስ | የፖስታ መላኪያ አድራሻ | ኢሜል/ድህረ-ገጽ |
|---|---|---|---|
| **የጤና ክፍል (DOH)** | **የጤና ክፍል ብቃት ማረጋገጫ አስተባባሪ (HCA Credentialing Coordinator)**<br>(360) 236-2700<br><br>**የጤና ክፍል ደንበኞች አገልግሎት**<br>(360) 236-4700 | **ማመልካቻውን የሚልኩት: (ክፍያ አያካቱ)**<br>DOH - Home Care Aide Credentialing<br>P.O. Box 1099<br>Olympia, WA 98507-1099<br>**ከመጀመሪያው ማመልከቻ ጋር ያልተላኩ ሌሎች ሰነዶችኘ ይላኩ፡**<br>DOH - Home Care Aide Credentialing<br>P.O. Box **47877**<br>Olympia, WA 98504-7877 | **የጤና ክፍል ድረ-ገፅ**<br>[የቤት እንክብካቤ ረዳት]<br><br>ጥያቄዎችን ለመመለስ እንዲረዳዎት የመረጃ መጽሄቱን (በ14 ቋንቋዎች) ያውርዱ:: |
| **ፕሮሜትሪክ** | **ስልክ ቁጥር፥**<br>1-800-324-4689 | **የፕሮሜትሪክ አድራሻ፡**<br>Attention: Washington Home Care Aide Program<br>7941 Corporate Dr.<br>Nottingham, MD 21236 | **የፕሮሜትሪክ ኢሜል፡**<br>WAHCA@prometric.com<br><br>ፕሮሜትሪክ የድር ጣቢያ:<br>ፕሮሜትሪክ |
| **የ HCA ፈጣን መገናኛዎች**: መገናኛዎችን በአንድ ቦታ **የቤት ውስጥ እንክብካቤ ድጋ ስልጠና አጭር መገናኛዎች** ላይ ያግኙ | | | |



# ክፍያ ማግኘት

## የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ አንድ መግቢያ (IPOne)

የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ አንድ (IPOne) በመባል የሚጠራው የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ አገልግሎት ለመጠየቅ እና ክፍያ ለማግኘት የሚጠቀሙበት ስርአት ነው፡፡ የ IPOne የተያዘው በህዝብ ሽርክና LLC (PPL) ነው፡፡

ክፍያ ለማግኘት እንክብካቤ በሰጡበት እያንዳንዱ ቀን የሰሩበትን ሰአት፣ ያጠናቀቁትን ስራ እና ርቀት (የሚተገበር ከሆነ) በጊዜ ማሳያ ወረቀት ላይ መጻፍ እና የጊዜ ማሳያ ወረቀቱን ለ IPOne ማስገባት አለብዎት፡፡ የጊዜ ሰንጠረዥዎትን በኤሌክትሪካዊ መንገድ በሚከተለው የ IPOne ፖርታል ላይ ማስገባት ይችላሉ፡ https://ipone.publicpartnerships.com/login.aspx እንዲሁም የጊዜ ማሳያ ወረቀቱን በፋክስ ወይም ፖስታ በመላክ ማስገባት ይችላሉ፡፡ IPOne ለመጠቀም ለመግባት፡

- www.ipone.org ይጎብኙ
- BetterOnline™ የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ
- 'መመዝብ' የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ እና የደህንነት ጥያቄዎቹን ይመልሱ

ክፍያ ለማግኘት የሰሩበትን ሰአት፣ ያጠናቀቁትን ስራ እና ርቀት ለ IPOne ማስገባት አለብዎት፡፡

ክፍያ ለማግኘት የሰሩበትን ሰአት፣ ያጠናቀቁትን ስራ እና ርቀት ለ IPOne ማስገባት አለብዎት፡፡

### የ IPOne ለመጠቀም የሚያገለግሉ ምንጮች

አዲስ የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ሆነው መስራት ሲጀምሩ የእንኳን ደህና መጡ እሽግ በፖስታ ያገኛሉ፡፡ የእንኳን ደህና መጡ እሽጉ የ IPOne ከ DSHS ያገኘው የእርስዎን የግል መረጃ የሚያሳይ ቅጽ ይይዛል፡፡ ይህ መረጃ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ድጋሚ ይመልከቱት፡፡ መረጃው ከተሳሳተ የ IPOne ለመጠቀም ከተመዘገቡ በኋላ ኦንላይን ያስተካክሉት ወይም የ IPOne የጥሪ ማዕከል ጋር በ844-240-1526 በመደወል ማስተካከያ ለማድረግ እርዳታ ማግኘት ይቻላል፡፡

እንዲሁም አዲስ የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ሆነው መስራት ሲጀምሩ ከ IPOne የስልጠና እሽግ ያገኛሉ፡፡ ይህ እሽግ የ IPOneን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ የሚረዳ መረጃ አለው፡፡

ስለ IPOne አጠቃቀም ለበለጠ መረጃ በሚከተለው የ IPOne ድህረ-ገጽ ይጎብኙ
www.publicpartnerships.com/programs/washington/IPOne/index.html

ሙሉውን የ IPOne የስልጠና መመሪያ ማውረድ ወይም የፈለጉትን ክፍል ብቻ ማየት ይችላሉ። በ IPOneን የጽሁፍ እና ኦንላይን ስልጠና መረጃው ውስጥ የተካተቱ ርዕሶች፡

- የተጠቃሚ ሂሳብ እንዴት እንደሚከፈት
- ክፍያ የሚያገኙበት ምርጫዎትን (ቀጥታ ማጠራቀሚያ ሂሳብ ማዘጋጀት) እንዴት እንደሚያዘጋጁ
- የግብር መረጃን እንዴት እንደሚያስተካክሉ እና እንደሚያረጋግጡ
- የ IPOne የይለፍ ቃል መለወጥ ወይም ማዘመን
- የፈቃድ መረጃዎችን እንዴት እንደሚያዩ
- የጊዜ ማሳያ ወረቀት እንዴት እንደሚያስገቡ (ለርቀት ካሳ ክፍያ እና ክፍያ ያለው ፈቃድ እና ቀጣይነት ያለው ትምህርተ ስልጠና እንዴት እንደሚገባ)
- የጊዜ ሰንጠረዥ ማስገቢያ ምልክቶች እና ምክሮች
- ያለፈ ክፍያ የተፈጸመበት የጊዜ ሰንጠረዥ ላይ ለውጥ ማድረግ
- የክፍያ መረጃ እንዴት እንደሚታይ
- ጥያቄ ካለ ማንን ማናገር እንዳለብዎት

## የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ አንድ የፈቃድ ደብዳቤ

የ IPOne በሚከተሉት ሁኔታዎች የፈቃድ ደብዳቤ ይልክልዎታል፡

- የቀጣሪዎት አገልግሎቶች መጀመሪያ ፈቃድ ሲያገኙ
- ፈቃዱ ላይ ተጽዕኖ የሚያመጣ ለውጥ ካለ

ይህንኑ ተመሳሳይ መረጃ ኦንላይን የ IPOne ሂሳብዎት ጋር በመሄድ ማየት ይችላሉ። ይህን እንዴት እንደሚያደርጉ ለማወቅ የ IPOne የስልጠና እሽግዎትን ያንብቡ።

## የተለወጡ መረጃዎችን ማሳወቅ

የስም፣ አድራሻ ወይም የባንክ ሂሳብ ለውጥ ካደረጉ የ IPOne ያነጋግሩ። የስልክ ቁጥር፣ አድራሻ ወይም የባንክ ሂሳብ ለውጦችን ኦንላይን የ IPOne ፖርታል ላይ ማሳወቅ ይችላሉ። የስም፣ የልደት ቀን ወይም የማህበራዊ ደህንነት ቁጥር ለውጥ ለማሳወቅ የደንበኛ አገልግሎት የጥሪ ማዕከል ጋር መደወል አለብዎት።

የ IPOne የደንበኛ አገልግሎት የጥሪ ማዕከል
844-240-1526

## ክፍያ ያለው ፈቃድ (PTO) ሰአታት

በፈለጉት መንገድ መጠቀም የሚችሉት ክፍያ ያለው ፈቃድ ማግኘት ይችላሉ። ምን ያህል ክፍያ ያለው ፈቃድ ማግኘት እንደሚችሉ በይበልጥ ለማወቅ ኦንላይን www.ofm.wa.gov/labor/agreements ላይ የሚገኘውን የ SEIU 775 አጠቃላይ የድርድር ህብረት ስምምነት ይመልከቱ።

### ክፍያ ያለው ፈቃድ ሰአትዎን ስለመጠቀም

ክፍያ ያለው ፈቃድ ሰአትዎን ከስራ እረፍት ለመውሰድ ወይም እረፍት ሳይወስዱ ገንዘቡ ለመውሰድ መጠቀም ይችላሉ። ክፍያ ያለው ፈቃድ ሰአትዎን በመጠቀም እረፍት መውሰድ ከፈለጉ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፡

- ቢያንስ ከሁለት ሳምንት በፊት ቀጣሪዎትን ማሳወቅ እና ፈቃድ ማግኘት።
- ቀጣሪዎት ጉዳይ ሀላፊ/ማህበራዊ ሰራተኛ እርስዎ ሳይኖሩ የእንክብካቤ እቅዱ አለመጓዱን ለማረጋጥ እንዲችል ይንገሩት/ሯት።

### ክፍያ ያለው ፈቃድ ሰአት የሚጠፋው መቼ ነው

ከፍተኛውን ክፍያ ያለው ፈቃድ ሰአት ከደረሱ ቀሪው ከከፍተኛ የሚፈቀድ መጠን በታች እስኪወርድ ድረስ ተጨማሪ ማግኘት/ማጠራቀም አይችሉም። ከዛ በላይ የሚጠራቀም ሰአት ይጠፋል። የሚፈቀደውን ከባለፈው የዞረ ክፍያ ያለው ፈቃድ ሰአታት ከፍተኛውን ለማወቅ እባክዎ የአሁኑን የህብረት የመደራደሪያ ስምምነት ይመልከቱ፣



## የስልጠና ሰአት

የስለጠና ሰአት ማለት የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ሆነው ለመስራት የሚያስፈልገውን ስልጠና ለማጠናቀቅ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያሳልፉት ጊዜ ነው። የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ አስፈላጊ ስልጠና ሰአት ካጠናቀቀ በኋላ እንዴት ክፍያ እንደሚጠይቅ እና እንደሚቀበል ለውጥ ተደርጓል።

> የስራ ሳምንቱ እሁድ 12:00 am ይጀምራል፤ በቀጣይ ቅዳሜ 11:59 pm ያበቃል።

### የስልጠና ክፍያ እንዴት እንደሚጠየቅ

ስልጠና ላይ ላለፈ ጊዜ ክፍያ የሚፈጸመው ስልጠናው በተደረገበት ቀን መሰረት ነው። ስልጠናው በተደረገበት የስራ ሳምንት በቀን የተጠናቀቁ የስልጠና ሰአታት መጠየቅ አለብዎት፤ የአገልግሎት ጊዜ በሚጠይቁበት መንገድ ያድርጉት። የስራ ሳምንቱ እሁድ 12:00 am ይጀምራል፤ በቀጣይ ቅዳሜ 11:59 pm ያበቃል።


## የትርፍ ሰአት ስራ ክፍያ እና ስራ ሳምንት ገደብ

ከኤፕሪል 3/2016 ጀምሮ DSHS የትርፍ ሰአት ስራ ክፍያን የሚያሰላው የግለሰብ አገልግሎት ሰጪዎች በስራ ሳምንት ውስጥ ከ40 ሰአት በላይ ሲሰሩ ነው። የትርፍ ሰአት ስራ ክፍያ ከመደበኛ የክፍያ መጠን 1.5 ጊዜ ይበልጣል።

የ IP የትርፍ ጊዜ ስራ ግብአት www.dshs.wa.gov/altsa/IPOT

የስራ ሳምንቱ እሁድ 12:00 am ይጀምራል፤ ቅዳሜ 11:59 pm ያበቃል።

የሳምንት ስራ የክፍያ ጊዜ እና የወሩ ጊዜ ሊያልፍ ይችላል። ከታች ያለውን ምሳሌ/ምስል ይመልከቱ።



## የስራ ሳምንት ገደብ ፍሬ ነገሮች

- የስራ ሳምንት ገደብ ማለት በስራ ሳምንት ውስጥ መስጠት የሚችሉት አጠቃላይ የአገልገሎት ሰአት ቁጥር ነው፡፡
- የስራ ሳምንት ገደብዎት ከፍታ ስራ ሳምንት ገደብ ካልተመደበልዎት ወይም DSHS ጊዜያዊ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር በሳምንት 40 አገልግሎት ሰአታት ነው፡፡
- በ DSHS ካልጸደቀ በስተቀር ከተመደበልዎት የስራ ሳምንት ገደብ በላይ መስራት አይችሉም፡፡

የአገልግሎት ሰአታት ወደ ስራ ሳምንት ገደብዎት ይቆጥራል፡፡ የአገልግሎት ሰአታት ማለት የሚከተሉትን በማድረግ ሚያልፍ ጊዜ ማለት ነው፡

- የግል እንክብካቤ
- የእፎይታ እንክብካቤ
- የክህሎት ማግኛ ስልጠና
- እረፍት ጊዜ አግልግሎት

## የስራ ሳምንት ገደብን ከተመደበ ሰአት ጋር ማስማማት

IPዎች ከተመደበላቸው የሳምንት የስራ ገደብ በላይ መስራት የለባቸውም እንዲሁም በወር ከተመደበላቸው የባለጉዳይ ሰአታት በላይ መስራት የለባቸውም፡፡

አገልገሎት በሚሰጡት ሰው የተመደበልዎትን ሰአታት DSHS ከሚመደብልዎት ስራ ሳምንት ገደብ ጋር መመጣጠኑን ማረጋገጥ የእርስዎ ሀላፊነት ነው፡፡

የሚከተሉትን የስራ ምደባዎች መቀበል አይችሉም፡

- ከስራ ሳምንት ገደብ በላይ መስራት
- ብቁ በሆኑ የስራ ቦታዎች መካከል ከ60 ደቂቃ በላይ መጓዝ
- በስራ ሳምንት ውስጥ ብቁ የሚያደርግ የጉዞ ሰአት ከ7 ሰአት በላይ መጠየቅ

## 40.25 ሰአታት እና ከዛ በላይ የሳምንት ስራ ገደብ ያላቸው IP የሳምንት ስራ ገደብ ተለዋዋጭነት

በ DSHS ካልጸደቀ በስተቀር በስራ ሳምንት ከተመደበልዎት ገደብ በላይ ሰአታት መስራት አይችሉም።

ለተወሰኑ ሁኔታዎች አገልገሎት የሚሰጡት ሰው ሳምንታዎ የስራ ሰአትዎን በአንድ ወር ውስጥ ባሉ ሳምንታት መካከል ሊያመቻች ይችላል፤ የሚከተሉት አራት ሁኔታዎች ከተሟሉ፡

1) በአንድ ሳምንት ውስጥ ተጨማሪ ሰአት የሚያስፈልገው የተወሰነ ፍላጎት ካለ
2) ከደንበኛው ወርሀዊ ሰአት በላይ የማይሰሩ ከሆነ
3) በአንድ ሳምንት ውስጥ ተጨማሪ አገልገሎት ሰአት መጠቀም በወሩ ውስጥ ባሉ ሌሎች ሳምንታት ውስጥ ደንበኛው ያለመሰረታዊ እንክብካቤ የማይቆይ ከሆነ
4) በወር ውስጥ ያሉትን ሰኣታት በእኩሌታ ተጠቅመው ቢሆን ኖሮ የሚሰሩትን የትርፍ ጊዜ ሰአት የማይሰሩ ከሆነ።

ደንበኛዎት ኒው ፍሪደም ወይም በጦር ሀይል የሚመራ የቤት አገልግሎት ተሳታፊ ከሆነ ከስራ ሳምንት ገደቡ በላይ ሰአት ለመግዛት ብቁ ባቸው። ለተጨማሪ መረጃ ደንበኛዎት የእንክብካቤ አማካሪያቸውን ማነጋገር አለባቸው።

## የደንበኛ ጤና እና ደህንነት አደጋዎችን ለመከላከል ከስራ ሳምንት ገደብዎት በላይ መስራት

የስራ ሳምንት ሰአትዎን በሙሉ ከሰሩበት እና በደንበኛ የጤና እና ደህንነት አደጋዎችን ምክንያት መቆየት ካስፈለገ የሚከተለውን ያድርጉ፡

a. ሁኔታው እስኪረጋጋ እና ደህና እስኪሆን ድረስ ከደንበኛው ጋር መቆየት።
b. የድንገተኛ ጊዜ ህክምና የሚያሻው አገልግሎት ድንገት ከተፈጠረ 9-1-1 ጋር ይደውሉ።
c. ተጨማሪ እገዛ በመፈለግ ደንበኛውን ያግዙ።
d. ሁኔታው ሲረጋጋ በቶሎ ስራዎትን ያቁሙ።
e. ስለሁኔታው ለማብራራት በሚቀጥለው የስራ ቀን የደንበኛውን የጉዳይ ሀላፊ ያነጋግሩ።

የስራ ፕሮግራምዎትን ከሚያሰሩዎት ሰው ጋር ማቀድ እና የስራ ሳምንት ገደብዎትን ወይም የተፈቀደ የጉዞ ጊዜዎትን አለማለፍዎትን ማረጋገጥ አብዎት።

## የጉዞ ጊዜ

ከአፕሪል 1/2016 ጀምሮ IPዎች ለጉዞ ሰአት ይከፈላቸዋል፡፡ የጉዞ ጊዜ ማለት በአንድ ቀን ውስጥ ከአንድ የስራ ቦታ ወደ ሌላ ሲጓዙ ነው፡፡ የጉዞ ጊዜ በሳምንታዊ አገልገሎት ሰአት ውስጥ አይቆጠርም፡፡

**የጉዞ ጊዜ ማለት፡**

- ከአንድ የስራ ቦታ ወደ ሌላ ቀጥታ አንድ የጉዞ ጊዜ፤ ሁለቱም የስራ ቦታ መኖሪያዎት መሆን የለበትም፡፡
- በስራ ቦታ እና በአስተማሪ የሚመራ የስልጠና ቦታ መካካል ቀጥታ የጉዞ ጊዜ፤ ሁለቱም የስራ ቦታ መኖሪያዎት መሆን የለበትም፡፡

**የስራ ቦታ ማለት፡**

- ለ DSHS ደንበኛ ፈቃድ ያለው አገልገሎት የሚሰጡበት ቦታ ነው፡፡
- አስፈላጊ ስልጠና የሚያገኙበት ቦታ

**የጉዞ ጊዜ ማለት የሚከተለው አይደለም፡**

- ከቤትዎ ወደ ስራ ቦታ ወይም ስልጠና ቦታ ጉዞ
- ከስራ ቦታ ወይም ስልጠና ወደ ቤትዎ ጉዞ
- ከግል እንቅስቃሴ ወደ ስራ ቦታ ወይም ስልጠና ቦታ ጉዞ

የተፈቃደ ጉዞ ጊዜ፣ አስፈላጊ የስልጠና ሰአት እና ክፍያ ያለው እረፍት በስራ ሳምንት ገደብ ውስጥ አይካተትም፡፡

በቤትዎ እና ስራ ቦታ መካከል ያለ የጉዞ ጊዜ ከሚንከባከቡት ሰው ጋር ሚኖሩ ቢሆንም እንኳን የጉዞ ጊዜ ክፍያ አያገኙም፡፡

የጉዞ መጠይቅ ቅጽ ከቀጣሪዎት የጉዳይ ሀላፊ ማግኘት ይቻላል፡፡

## የጉዞ ጊዜ እንዴት እንደሚጠየቅ

የጉዞ ጊዜ ለመጠየቅ የሚሳ የጉዞ ጊዜ መጠየቂያ ቅጽ ለቀጣሪዎት ጉዳይ ሀላፊ ያስገቡ፡፡ ከተቻለ ይህን ቅጽ የጉዞ ጊዜው ከመከናወኑ በፊት ያስገቡ፡፡ ያልታቀደ የጉዞ ጊዜ ካጋጠመዎት የቀጣሪዎትን ጉዳይ ሀላፊ ወዲያው ማነጋገር እና የጉዞ ጊዜ መጠይቅ ቅጽ ማስገባት አለብዎት፡፡

የደንበኛው ጉዳይ ሀላፊ የጉዞ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈል ፈቃድ ይሰጣል፡፡ ለክፍያ የደረሰ የጉዞ ጊዜ የሚጸድቀው ከሚከተሉት ሳይበልጥ ነው፡

- ብቁ በሆኑ የስራ ቦታዎች መካከል 60 ደቂቃ ወይም
- በስራ ሳምንት ውስጥ 7 ሰአት

የጉዞ ጊዜዎትን የሚጠይቁት በ IPOne ስርአት ላይ ጉዞው በተከናወነበት ቀን መሰረት ነው፡፡ የ IPOne ፖርታል ወይም በጊየ ማሳያ ወረቀት ላይ ሰአቱን በማስገባት መጠየቅ ይችላሉ፡፡

## ከልክ ያለፈ መጠይቅ እና የውል እርምጃዎች

የሚከተለውን በሚያስከትል መልኩ ስራ እና የስራ ሰአታት ከተቀበሉ

- ከልክ ያለፈ የትርፍ ሰአት ስራ
- ከባለጉዳዩ ወርሀዊ ሰአታት በላይ መስራት
- ያለመምሪያው ፈቃድ የጉዞ ገደብ ፈቃድ በላይ መሄድ (ገጽ 22 ይመልከቱ)

....የውል እርምጃ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ከትርፍ ሰአት ጋር የተያያዘ ከሶስት ውል እርምጃዎች በኋላ ውልዎት ይቋረጣል፡፡ ይህ ከሆነ አዲስ ውል ለማድረግ 90 ቀን መጠበቅ አለብዎት፡፡ የስራ ሳምንትዎትን ወይም የጉዞ ጊዜዎትን ጉልህ በሆነ መልኩ በተደጋጋሚ ካለፉ IP ሆነው ድጋሚ ውል ለማድረግ አይችሉም፡፡

### ከስራ ሳምንት ገደብ በለይ ለአሚሰርዋቸው ስራዎች የውል እርምጃዎች አያገኙም:

- የDSHS ስልጠና አስፈላጊ ነው
- የጸደቀው የጉዞ ጊዜ
- አስተዳደራዊ ጊዜ
- ክፍያ ያለው ፈቃድ (PTO) ሰአታት

**የውል እርምጃዎችን እንዴት ማስቀረት እችላለሁ?**

- ሁልጊዜ የስራ ፕሮግራምዎትን አስቀድመው ያቅዱ እና ይጻፉት።
- የደንበኛው ፍላጎት ከተቀየረ እና የስራ ሳምንት ገደብዎን ሊያስተጓጉል የሚችል ሌላ አይነት ፕሮግራም መስራት ካለብዎት የደንበኛውን የጉዳይ ሀላፊ በቶሎ ያነጋግሩ።
- ሁልቀን ከስራ በኋላ የጊዜ ወረቀትዎ ላይ የስራ ሰአትዎን ይጻፉ፤ እንዲሁም በወረቀት የቀን መቁጠሪያ ላይ መጻፍ ይረዳል። በWWLዎት ውስጥ እንደሆኑ ለማወቅ ተሎ ሎ ያረጋግጡ።
- በWWLዎት ውስጥ እንዲሆኑ ፕሮግራምዎትን እንዴት ማድረግ እንዳለብዎት ለማወቅ እርስዎን እና ቀጣሪዎት/ደንበኛውን የሚረዳ የመረጃ ምንጭ DSHS አለው። የመረጃ ምንጮቹ www.dshs.wa.gov/altsa/IPOT ላይ ይገኛሉ።

**የውል እርምጃ በውል መዝገቤ ላይ ምን ያህል ጊዜ ይቆያል?**

እያንዳንዱ የውል እርምጃ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ12 ወራት ክፍት ሆኖ ይቆያል። ከ12 ወራት በኋላ የውል እርምጃው ይዘጋል።

**በውሉ ተግባራት ወይም የተሰጠው ደብዳቤ የተገለጸው ወር የደሞዝ መክፈያ ወር ነው:**

- ለምሳሌ ደብዳቤው "ይህ የውል እርምጃ የተወሰደው በአፕሪል ወር ለተከፈለ ሰአታት ነው" ካለ ይህ ማለት ቀደም ብሎ በነበረው ወር (ማርች) ለሰሩት የጤቁት ሰአታት በአፕሪል ተከፍሎዎታል ነው።
- አላፊ ስለጠየቁበት ወር ጥያቄ ካልዎት እባክዎ የጉዳይ ኃላፊን ያንገሩ።



## የጉዞ ካሳ ክፍያ

የጉዞ ካሳ ክፍያ ከጉዞ ጊዜ ይለያል፡፡ የጉዞ ካሳ ክፍያ ማለት ለቀጣሪዎት መሰረታዊ አስቤዛ ለመሸመት ወይም ቀጣሪዎትን ለህክምና አገልግሎት ለመውሰድ በግል መኪናዎት ለነዱት ርቀት መከፈል ማለት ነው፡፡

- የጉዞ ካሳ ክፍያ ለማግኘት መሰራዊ አስቤዛ መግዛት ወይም ለህክምና መጓጓዣ አገልግሎት የቀጣሪዎት የእንክብካቤ እቅድ መሆን አለበት፡፡
- የጉዞ ካሳ ክፍያ መጠን ለእያንዳዱ ቀጣሪ በአንድ ወር እስከ 100 ማይል ርቀት ሊሆን ይችላል፡፡
- ደንበኛን በራስዎት መኪና ለማሽርከር ከመረጡ የግዛቱ ህግ በመሚያዘው መሰረት ትክክለኛ/ወቅታዊ የግዛቱ የመንጃ ፈቃድ እና የመድህን ሽፋን ሊኖርዎት ይገባል፡፡

የ DSHS ደንበኛን እንክብካቤ በሚያግዘው መርሀግብር መሰረት አንዳንድ ግለሰብ አገልግሎት ሰጪዎች ሌላ የመጓጓዣ አገልገሎት ለሰጡት ለተጨማሪ ርቀት ካሳ ክፍያ ያገኛሉ፡፡ ተጨማሪ የመጓጓዣ ፍላጎት፤ ለምሳሌ ቀጣሪን ወደስራ መውሰድ ግን በእንክብካቤ እቅዱ ላይ በግልጽ መቀመጥ እና ለግለሰብ አገልግሎት ሰጪው መመደብ አለበት፡፡ በዚህ ሁኔታ ብቻ ግለሰብ አገልግሎት ሰጪው ለተጨማሪ ርቀት በእንክብካቤ እቅዱ ላይ በጉዳይ ሀላፊው እስከተፈቀደው መጠን ድረስ ካሳ ሊከፈለው ይችላል፡፡

## ደሞዝ እና የክፍያ ጭማሬ

የ IPዎች መነሻ የሰአት መጠን በ DSHS እና SEIU 775 መካከል ድርድር በተደረገበት የህብረት የድርድር ስምምነት መሰረት ነው፡፡ ከጃንዋሪ 1/2019 ጀምሮ የሰአት መጠን ከ$15.00 ጀምሮ ሲሆን ጭማሬዎች የሚያያዙት ከአጠቃላይ የስራ ሰአትዎት ጋር ነው፡፡ ለ2017-19 የመጨረሻዎቹ የስድስት ወራት ክፍሎች የድርድር ወቅት የሰአት መጠን የክፍያ ሰንጠረዡ ላይ ይታያል፤ ለጃንዋሪ 1/2019 - ጁን 30/2019፡፡ እነዚህ ሰንጠረዦች በሂሳብ አስተዳደር ጽ/ቤት ድህረ-ገጽ www.ofm.wa.gov/state-human-resources/labor-relations/collective-bargaining-agreements ላይ በሚገኘው የህብረት የድርድር ስምምነት አባሪ ሀ ላይ ይገኛል፡፡ የወደፊት ክፍያ በወደፊት ስምመነት ላይ ይገለጸል፡፡

አንዳንድ ግለሰብ አገልገሎት ሰጪዎች በህብረት የድርድር ስምምነቱ መሰረት የተወሰኑ የማረጋገጫ ወይም ነጻ ማድረጊያ መስፈርት ሲያሟሉ ማረጋገጫ ለማግኘት እና/ወይም ከፍተኛ ስልጠና የተለያየ ክፍያ ለማግኘት ብቁ ናቸው፡፡

# ተቀናሽ ግብር እና ክፍያ

## የፌደራል የገቢ ግብር

ከክፍያዎት ላይ ትክክለኛው የፌደራል ገቢ ግብር እንዲቆረጥ የ W-4 የግብር ቅጽ ሞልተው ያስገቡ። የ W-4 የግብር ቅጽ ካላስገቡ የግብር ማስገቢያ ሁኔታዎት "ነጠላ" ከ"0" አበል ጋር ይሆናል። ይህ ከፍተኛው ተቆራጭ ግብር ደረጃ ሲሆን ከክፍያዎት ላይ ከፍተኛው የግብር መጠን ይቀነስብዎታል።

ከክፍያዎት ላይ ተጨማሪ የፌደራል ገቢ ግብር መጠን እንዲቀነስ ከፈለጉ ከገቢዎት ላይ ተጨማሪ የፌደራል ገቢ ግብር መጠን እንዲቀነስ በመግለጽ የ W-4 ቅጽ ሞልተው እና ፈርመው ያስገቡ።

ከሚቀነሰው ላይ መተው ከጠየቁ ("የተተወ") ለዚህ አመት መተዉ በሚቀጥለው አመት ፌብሩዋሪ 15 ላይ ያበቃል። "የተተወ" ሆኖ ለመቆየት በእያንዳንዱ አመት አዲስ ቅጽ ማስገባት አለብዎት። አዲስ የ W-4 ቅጽ ካላስገቡ የግብር ማስገቢያ ሁኔታዎት "ነጠላ" ከ"0" አበል ጋር ይሆናል።

የተሞላውን እና የተፈረመውን ቅጽ ለሚከተለው ይመልሱ፡

- ለ IPOne በሚከተለው ኢሜል ያድርጉ pplwaipone-cs@pcgus.com
- ለ IPOne በሚከተለው ፋክስ ያድርጉ 1-855-901-6904

***ማስታወሻ፡ እባክዎ ለመህደሩ ያስገቡትን የW-4 ቅጽ ቅጂውን ያስቀምጡ***

## W-4ን መሙላት

የ IRS W-4 ቅጽ በሚከተለው መንገድ ማግኘት ይቻላል፡

- ከ IRS በሚከተለው ላይ ቅጹን ያውርዱ www.irs.gov/pub/irs-pdf/fw4.pdf
- IRS ጋር በ 1-800-829-3676 መደወል እና ቅጽ እንዲላክልዎት መጠየቅ።

ሳጥን 1፣ 2፣ 3 እና 5 ግዴታ መሞላት አለባቸው። ሳጥን 4፣6 እና 7 መሙላት ግዴታ አይደለም። ሳጥን 8፣ 9 እና 10 ክፍት ይተዉት፡፤ "የሰራተኛ ፊርማ" እና "ቀን" በሚለው በገጹ ስር ፈርመው ቀን መጻፍዎትን ያረጋግጡ።

**የተሞላውን የ IRS W-4 ቅጽ በሚከተለው በፖስታ ወይም ፋክስ ይላኩ፡**

ነጻ ፋክስ #1-855-901-6904

Public Partnerships, LLC: WA IPOne
7776 S Pointe Pkwy W Suite 150
Phoenix, AZ 85044

Separate here and give Form W-4 to your employer. Keep the worksheet(s) for your records.

Form **W-4**
Department of the Treasury
Internal Revenue Service

**Employee's Withholding Allowance Certificate**

▶ Whether you're entitled to claim a certain number of allowances or exemption from withholding is subject to review by the IRS. Your employer may be required to send a copy of this form to the IRS.

OMB No. 1545-0074

**2019**

| | | |
|---|---|---|
| 1 Your first name and middle initial | Last name | 2 Your social security number |
| Home address (number and street or rural route) | 3 ☐ Single ☐ Married ☐ Married, but withhold at higher Single rate. Note: If married filing separately, check "Married, but withhold at higher Single rate." | |
| City or town, state, and ZIP code | 4 If your last name differs from that shown on your social security card, check here. You must call 800-772-1213 for a replacement card. ▶ ☐ | |

5 Total number of allowances you're claiming (from the applicable worksheet on the following pages) . . . . 5

6 Additional amount, if any, you want withheld from each paycheck . . . . . . . . . . . . . . . 6 $

7 I claim exemption from withholding for 2019, and I certify that I meet **both** of the following conditions for exemption.
• Last year I had a right to a refund of **all** federal income tax withheld because I had **no** tax liability, **and**
• This year I expect a refund of **all** federal income tax withheld because I expect to have **no** tax liability.
If you meet both conditions, write "Exempt" here . . . . . . . . . . . . . . . . ▶ 7

Under penalties of perjury, I declare that I have examined this certificate and, to the best of my knowledge and belief, it is true, correct, and complete.

**Employee's signature**
(This form is not valid unless you sign it.) ▶ **Date ▶**

| | | |
|---|---|---|
| 8 Employer's name and address (**Employer:** Complete boxes 8 and 10 if sending to IRS and complete boxes 8, 9, and 10 if sending to State Directory of New Hires.) | 9 First date of employment | 10 Employer identification number (EIN) |

በቀድሞው ግዜ የፌደራል የገቢ ግብሩን በጉልህ ከሚገባው በታች የያዙ እንደሆነ ÷የተወሰነ መጠን ያለው የፌደራል ገቢ ግብር እንዲያዝ IRS እርስዎን እና PPLን በደብዳቤ(“Lock-in Letter” ይባላል) ሊያስታውቅ ይችላል፡፡ እንደዚህ ከሆነ ከ IRS ተጨማሪ ማስታወቂያ እስኪደርሳቸው ድረስ DSHS እና PPL መፈጸም አለባቸው፡፡ ከ IRS Lock-in ደብዳቤ የደረስዎት ከሆነ ÷ ለመቃወም ከፈለጉ ሊደውሉ የሚችሉበት ከክፍያ ነፃ የስልክ ቁጥር ይኖረዋል፡፡

ጥያቄ ካለዎት እባክዎ የ IPOne የጥሪ ማዕከል 844-240-1526 ላይ ይደውሉ፡፡ የ IPOne ወይም DSHS ሰራተኞች የግብር ባለሙያዎች እንዳልሆኑ እና የግብር ምክር መስጠት እንደማይችሉ እባክዎ ያስተውሉ፡፡ የግብር ውሳኔዎችን ሲወስኑ የDSHS ወይም PPL ሰራተኞችን እርዳታ አይጠይቁ፡፡ የጥያቄዎት ምላሽ የግብር ምክር የሚያስፈልገው ከሆነ የግብር አማካሪ፣ የሂሳብ ሰራተኛ ወይም ከ IRS ምክር እንዲያገኙ ይመራሉ፡፡ SEIU 775 እና አንዳንድ የማህበረሰብ ድርጅቶች ነፃ የግብር ድጋፍ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

## እንክብካቤ መስጠት አስቸጋሪ ሲሆን ገቢን ማውጣት

ከባጉዳይ ጋር የሚኖሩ IP ከሆኑ የእንክብካቤ አገልግሎት በመስጠት የሚያገኙት ገቢ ከፌደራል የገቢ ግብር (FIT) ሊወጣ ይችላል፡፡

IP ከ DSHS ባለጉዳይ ጋር በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖር ከሆነ ግለሰብ አገልግሎት ሰጪዎች እንክብካቤ መስጠት አስቸጋሪ ሲሆን ገቢን ለማውጣት ብቁ ይሆናሉ፡፡ ይህ ማለት IPዎች አብረዋቸው ለሚኖሩ የ DSHS ባለጉዳይ እንክብካቤ ሰጥተው የሚያገኙት ገቢ ለገቢ ግብር አላማ ከ IPው ገቢ ላይ ይወጣል፡፡

እንክብካቤ መስጠት አስቸጋሪ ሲሆን ገቢን ማውጣት የሚተገበረው በአመት መጨረሻ የገቢ መግለጫ ላይ ተለይተው የተዘረዘሩ የግል እንክብካቤ አገልግሎቶች እና የእፎይታ እንክብካቤ ብቻ ነው፡፡ የእፎይታ እንክብካቤ፣ ችሎታ መማሪያ ስልጠና፣ የጉዞ ሰአት፣ አስፈላጊ ስልጠናዎች ወይም ክፍያ ያለው የእረፍት ጊዜ ላይ የገቢ ማውጣቱ አይተገበርም፡፡ የገቢ ማውጣቱ "ተሳትፎ" ወይም "የባለጉዳይ ሀላፊነት" ተብለው የሚታወቁ ከባለጉዳዩ በቀጥታ የሚያገኙት ክፍያ ላይ አይተገበርም፡፡

ይህ የገቢ ማውጣቱ እርስዎ ላይ እንደሚተገበር ማወቅ የእርስዎ ሀላፊነት ነው፡፡ እንዲሁም የትኞቹ ክፍያዎች ለግል እንክብካቤ አገልግሎት ወይም ለእፎይታ እንክብከቤ እንደሆኑ ማወቅ እና የግብር ተመላሽዎትን ከአጠቃላ ገቢዎት ላይ እነዛን ብቻ ማውጣት የእርስዎ ሀላፊነት ነው፡፡ ስለብቁነትዎ ወይም የአመቱ መጨረሻ የግብር ተመላሽ እንዴት እንደሚገባ ጥያቄ ካለዎት ወይም እገዛ ከፈለጉ እባክዎ የግብር ባለሙያ ወይም IRSን ያነጋግሩ፡፡

ጥያቄ ካለዎት እባክዎ www.dshs.wa.gov/altsa/irs-notice-2014-7-difficulty-care-payments-excludable-income ላይ ይመልከቱ ወይም የ DSHS የግብር ዴስክን በሚከተለው ያነጋግሩ፡

(866) 563-8155 (ነጻ መስመር)

(360) 664-5830 (Lacey/Olympia)

taxinfo@dshs.wa.gov

## W-2 የደሞዝ መግለጫ

የW-2 ቅጽ ግብር የሚከፈልበትን የገቢዎን ክፍል ለፌደራል እና የግዛት መንግስታት የሚያስታውቅ የደሞዝ መግለጫ ነው፡፡ በዚያ ዓመት ላገኙዋቸው ለእያንዳንዳቸው አሰሪዎች የ W-2 የደሞዝ መግለጫ እና ለዕረፍት ግዜ ክፍያዎ W-2 ይደርሶታል፡፡  አንዳድ IPዎች ከ2016 በፊት የተገኘ እና “Pseudo ባለጉዳይ” ለሚል የእረፍት ክፍያ W-2 ይሰጣቸዋል፡፡

የ W-2 ደሞዝ መግለጫዎች ጃንዋሪ 31 ከማለፉ በፊት(ወይም ጃንዋሪ 31 የሚያርፈው በሳምንቱ መጨረሻ/በዓል ላይ ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን) ክፍያ ባገኙበት ዓመት በ PPL በፖስታ ይላካሉ፡፡ ለምሳሌ በ2018 ገቢ የተከፈሎት ከሆነ ለነዚያ ገቢዎች የ W-2 ቅጾ ጃንዋሪ 31/2019 በፖስታ ይላክሎታል፡፡ በእያንዳንዱ አገልግሎት ሰጪ ፕሮፋይል IPOne ላይ የ W2 ኤሌክትሪካዊ ቅጂ ተለጥፏል፡፡

የ W-2 ደሞዝ መግለጫዎች በ IPOne የክፍያ ስርዓት አማካኝነት የተቀበሏቸውን ክፍያዎች ያካትታሉ፡፡ ከቀጣሪዎ በቀጥታ የሚቀበሉት ደሞዝ በሚቀበሉት የ W-2 ደሞዝ መግለጫ ላይ አይካተትም፡፡ መዝገብዎ ላይ ባለው የ W-4 ቅጽ መሰረት ለፌደራ የገቢ ግብር የሚቀነሰው መጠን በ W-2 ቅጽዎት ላይ ይታያል፡፡ ከ PPL ስለተቀበሉት W-2 ጥያቄ ካሎት IPOne የጥሪ ማዕከል 844-240-1526 ላይ ይደውሉ፡፡ የ IPOne ሰራኞች የግብር ምክር መስጠት አይችሉም፤ የግብር አማካሪ ወይም ባለሙያ፣ የሂሳብ ሰራተኛ ወይም IRS እንዲያናግሩ ይመሩዎታል፡፡

## የማህበራዊ ዋስትና እና የአዛውንቶች ህክምና ግብሮች

ምንም እንኳ PPL ቀጣሪዎ ባይሆንም ስለቀጣሪዎ በ PPL ከተከፈልዎት ገቢዎች PPL የመያዣ እና የማህበራዊ ዋስትና እና የአዛውንቶች ህክምና ግብር (FICA) ክፍያ ኃላፊ ነው።

በእድሜዎ ፥ ተማሪ በመሆንዎ ወይም ከቀጣሪው ጋር ባሎት ቤተሰባዊ ግንኙነት ምክንያት ከማህበራዊ ዋስትና እና ስራ አጥነት ግብር ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ። ነፃ መሆንዎን ለማረጋገጥ ለ IPOne የጥሪ ማዕከል ይደውሉ ወይም ከ www.publicpartnerships.com/programs/washington/ipone/index.html በዕድሜ ፥ በተማሪነት ፥ እና በቤተሰባዊ ግንኙነት መሰረት ከቅጥር ግብር ነፃ የመሆንን ማመልከቻ ያውርዱ።

በፌደራል ህግ ስር ይህ ነፃ መሆን አማራጭ አይደለም። ከግብር ነፃ ለመሆን መስፈርቶቹን የሚያሟሉ ከሆነ ከእያንደንዱ እንክብካቤ ለሚያደርጉለት ሰው ቅጽ ይሙሉ እና ቅጹን ለ IPOne ይልካሉ።

- ጥያቄዎች ወይም ያሳሰቡዎት ጉዳዮች ካሉ www.irs.gov ላይ IRS ን ማግኘት ወይም የአካባቢ ጽ/ቤትዎን መጎብኘት ይችላሉ።.
- በተጨማሪ PPL ለፌደራል እና የግዛት ስራ አጥነት ግብር (FUTA/SUTA) ክፍያ ኃላፊነት አለበት።
- እንዲሁም ቀጣሪዎ በቀጥታ ከሚከፍልዎት መጠን ላይ የማህበራዊ ደህንነት እና የአዛውንቶች ህክምና ግብር ቀንሶ ለማስቀረት ኃላፊነት ሊኖርበት ይችላል።

IPOne መረጃ ማዕከል አባላት ሊመልሱ የሚችሉት በPPL ስለተሰጥዎት W-2ዎች ብቻ ነው። IPOne መረጃ ማዕከል አባላት ስለ ግብር ምክር ለመስጠት አይገኙም።



# አጠቃላይ የቅጥር መረጃ

## የጤና መድን አማራጮች

ሁለት የጤና ኢንሹራንስ አማራጮች አሉዎት፡ በ Washington Health Benefit Exchange በኩል የሚዘጋጁት SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን ወይም የጤና ኢንሹራንስ አማራጮች፡፡ **ከነዚህ በአንደኛው የጤና ዕቅዶች ብቻ መሳተፍ ይችላሉ፡፡**

## SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን

SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን ብቁ ለሆኑ IPዎች የሰራተኛ-ብቻ ህክምና፣ የጥርስ፣ የታዘዘ መድሀኒት፣ የእይታ፣ የመስማት፣ የሰራተኛ ድጋፍ መርሀግብር (EAP) እና የባህሪይ የጤና ጥቅሞች ይሰጣል፡፡ SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን ለባል/ሚስት ወይም ተረጂዎች ሽፋን አይሰጥም፡፡ ለ Medicare ብቁ IPዎች በ SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን በኩል እንደ ተቀዳሚ ሽፋን ሽፋን ይገኛል፡፡

የጤና እንክብካቤ ጥቅሞች ምዝገባ እና ብቁነት መስፈርቶች በ SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን ይወሰናሉ፡፡ ወቅታዊው ዝቅተኛ መስፈርቶች እርስዎ:

- በሌላ ቤተሰብ ሽፋን ወይም ሌላ ቀጣሪ-ተኮር ሽፈን በኩል የጤና እንክብካቤ ጥቅሞች ካላገኙ፡፡
- ቢያንስ ለሁለት ተከታታይ ወራት በትንሹ በወር ለ80 ሰዓታት ከሰሩ፡፡ ይህም የተሰራባቸውን እና መብት የተጠየቀባቸውን ሰዓታት ያጠቃልላል ለምሳሌ የስልጠና ሰዓታት ÷ የእረፍትሰዓታት ÷ እና እንደ እንደራሴ አቅራቢ የተሰራባቸውን ሰዓታት፡፡
- ከገቡ በኋላ ከመደበኛ ክፍያዎት ላይ የሚቀነስ የጤና እንክብካቤ ሽፋን ወርሀዊ የጋራ-አረቦን $25.00 ከከፈሉ፡፡
- የምዝገባ ማመልከቻ ካሟሉ እና ለ SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን ከሰጡ፡፡ የአባል ግብዐት ማእከል (MRC) 1-866-371-3200 ላይ በመደወል ወይም ኦንላይን www.myseiubenefits.org/ ላይ የምዝገባ ማመልከቻ ያገኛሉ፡፡ ለጤና እንክብካቤ ሽፋን ብቁ ከሆኑ SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን ማመልከቻ ይልከልዎታል፡፡ ማመልከቻው የሚላከው IPOne መዝገብ ላይ ባለው አድራሻ ነው፡፡
- ሁለት ተከታታይ ወራት በ80 ሰአታት ከሰሩ፣ የአንድ ወር የአስተዳደር ወቅት ከተፈቀደ በኋላ በአራተኛው ወር የመጀመሪያ ቀን ሽፋን ከዛ ይጀምራል፡፡ በተጨማሪ ቀጣይነት ላለው ሽፋን በወር 80 ሰአታት መስራት መቀጠል አለብዎት፡፡

የጤና ጥበቃ መድን ሽፋንዎን መስተጓጎል ለማስቀረት በየወሩ በ IPOne አማካኝነት የስራ ሰዓትዎን በወቅቱ መጠየቅ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ እባክዎ ሰአታትዎን በተቻለ መጠን ቀደም ብለው ይመዝግቡ፡፡ ስለ ተገቢነት መስፈርቶች እና ጥቅሞች ወይም የመመዝገቢያ ማመልከቻ ለመጠየቅ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን 1-(866) 371-3200 ለአባላት መረጃ ማዕከል ይደውሉ፡፡

## Washington Health Benefit Exchange

የጤና መድን ሽፋን በ Washington Health Benefit Exchange አማካኝነትም ይገኛል፡፡ በሚኖሩበት ስፍራ ወይም በግለሰባዊ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት ቁጥር ያላቸው ለአቅምዎ የሚመጥኑ የጤና ዕቅድ አማራጮች ሊቀርቡልዎ ይችላሉ፡፡ ስለ Washington Health Benefit Exchange አማራጮች ተጨማሪ መረጃ ወይም ሽፋን ለማግኘት ለማመልከት www.wahealthplanfinder.org ላይ የ Health Plan Finder ን ድረገጽ ይጎብኙ፡፡

ጥያቄዎች ካሎት÷ 1-855 923-4633 ላይ ከሰኞ - አርብ 7:30 a.m. - 8:00 p.m ለደንበኞች ድጋፍ ማዕከል ይደውሉ፡፡ ቁጥር ባላቸው ቋንቋዎች እርዳታ ተዘጋጅቷል፡፡

ስለማመልከቻው ወይም የጤና እቅድዎትን አማራጮች ለመረዳት እርዳታ ከፈለጉ የተመዘገቡ ደላሎች እና ማረጋገጫ ያላቸው አፋላጊዎች በተለያዩ ቋንቋዎች ለመርዳት ዝግጁ ናቸው፡፡

- የተመዘገበ ደላላ ለማግኘት የደላላ አፋላጊ ድህረ-ገጽ ይጎብኙ www.wahealthplanfinder.org/HBEWeb/Annon_DisplayBrokerNavigatorSearch.action?brokerNavigator=BRK
- ማረጋገጫ ያለው አፋላጊ ለማግኘት የአፋላጊ ድህረ-ገጽ www.wahealthplanfinder.org/HBEWeb/Annon_DisplayBrokerNavigatorSearch.action?brokerNavigator=NAV ላይ ይጎብኙ



## ጡረታ

አንዳንድ IPዎች በጡረታ ትረስ በኩል ለሚሰጠው የጡረታ ጥቅማ-ጥቅመ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ እና ስሌላም የበለጠ መረጃ ለማግኘት የአባል ግብአት ማዕከልን (MRC) 1-866-371-3200 ላይ ያነጋግሩ።

## ተጨማሪ ደንበኛ ማግኘት

**የቤት እንክብካቤ ምሪት ምዛገባ** ብቁ የሆኑ የአገልግሎት ሰጪዎችን የረዥም ጊዜ እንክብካቤ አገልግሎት ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር ለማገናኘት ድህረ-ገጽ ተኮር እና ኦንላይን መሳሪያ ይጠቀማል። የጥቆማ መዝገብ ውስጥ መግባት ቀላል ነው። ሂደቱን ለመጀመር አካባቢያዊ የምዝገባ ጽ/ቤት ይደውሉ ወይም ይሂዱ። አካባቢያዊ የጥቆማ መዝገባ ጽ/ቤት በ1-800-970-5456 በመደወል ወይም www.hcrr.wa.gov በመጎብኘት እና "የምዝገባ ጽ/ቤቶች" የሚለውን በመጫን በእርስዎ አካባቢ የጥቆማ ምዝገባው እንደሚገኝ ማየት ይችላሉ።

የጥቆማ ምዝገባው ማዕከል የሚሰሩ ሰራተኞች ሰዎች ግለሰብ አገልገሎት ሰጪ ሆነው መስራት እንዲጀምሩ ይረዳሉ።

**Carina** ማረጋገጫ ያላቸው ግለሰብ አገልግሎት ሰጪዎችን እና የ የቤት ውስጥ የእንክብካቤ ባለጉዳዮችን እንዲገናኙ ለመርዳት የተፈጠረ ነጻ ራስን የማገልገያ ድህረ-ገጽ ነው። ይህን አገልግሎት ለመስጠት Carina ከ SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን እና DSHS ጋር በጋራ ይሰራል። ሲጎበኙ የሚከተሉትን ደረጃዎች ይከተሉ፡ www.carinacare.com

- ደረጃ 1: መመዝገብ - "መመዝገብ" የሚለውን ቁልፍ በመጫን እና ጥቂት ጥያቄዎች በመመለስ የ Carina ሂሳብዎን ያስጀምሩ።
- ደረጃ 2: የቀረቡ ስራዎች እና የሰዎችን ታክ/ማንነት ያዛምዱ - ይመልከቱ። ፍላጎትዎን የሚያሟላ አገልግሎት ሰጪ ወይም ባለጉዳይ ጋር ይገናኙ፡
- ደረጃ 3: ፈቃድ - የአገልግሎት ሰጪዎን ፈቃድ ለማጠቀቅ እና ስራ ለመጀመር የጉዳይ ሀላፊዎት ጋር ይደውሉ።

### ለአገልግሎት ሰጪዎች ምንጮች

ለግለሰብ አገልግሎት ሰጪዎች መረጃ እና እርዳታ ኦንላይን የቤት ውስጥ እንክብካቤ የጥቆማ ምዝገባ ድህረ-ገጽ ላይ ይገኛል፡፡ ስለበሽታዎች እና ሁኔታዎች፣ የእንክብካቤ ምክሮች፣ ዜና እና የአገልግሎት ሰጪዎች ርእሶች ላይ የተሻሻለ መረጃ ለማግኘት የአገልግሎት ሰጪዎች ምንጮች የሚለውን ይጫኑ፡፡

## የሰራተኛ ካሳ

ግለሰብ አገልግሎት ሰጪዎች በ Washington ግዛት የሰራተኛ እና ኢንዱስትሪ መምሪያ በኩል የሰራተኛ ካሳ መድህን ሽፋን አላቸው፡፡ ይህ ማለት ለማንኛውም ከስራ ጋር የተያያዘ ህመም ወይም ጉዳት ጥቅም መጠየቅ ይችላሉ፡፡

ለቀጣሪዎት አገልግሎት ሲሰጡ ከተጎዱ እና አስቸኳይ ህክምና ካስፈለገዎት በአካባቢው ወደሚገኛ ሆስታል ወይም መደበኛ ሀኪምዎት ጋር ይሂዱ፡፡ ህመምዎት ወይም ጉዳቱ ከስራ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ለሀኪሙ ይንገሩት እንዲሁም "የጉዳት ሪፖርት ወይም የስራ ላይ በሽታ" ቅጽ ጠይቀው መሙላት እንዳይረሱ፡፡ ቅጹ ላይ ቀጣሪዎትን ይዘርዝሩ HCQA Negotiated Contract, 601 Union St., Suite 3500, Seattle, WA 98101፡፡

Sedgwick CMS የሚባል ኩባንያ የግለሰብ አገልገሎት ሰጪ ሁሉንም የሰራተኞች ካሳ ጥያቄዎች ያስተናግዳል፡፡ በስራ ላይ ከተጎዱ በነጻ መስመር በ 1-866-897-0386 ያነጋግሯቸው፡፡



## መግለጫ፣ የቅጥር ማረጋገጫ፣ የገቢ ማስረጃ

### የስራ መግለጫ

ለእርስዎ የስራ መግለጫ መስጠት የቀጣሪዎት ምርጫ ነው። የጽሁፍ የስራ መግለጫ ከቀጣሪዎት ማግኘቱ ይመረጣል። የጽሁፍ የስራ መግለጫ ቀጣሪዎት መስጠት በሚችልበት ሁኔታ ለማግኘት ይሞክሩ። ለቀጣሪዎት አሁን ለመልቀቅ እንደማያስቡ ነገር ግን ወደፊትን እንደሚያስቡ ያሳውቁ።

### የቅጥር ማረጋገጫ

የስራ ቅጥርዎትን ለማረጋገጥ የሚፈልጉ ሰዎች ቀጣሪዎትን ማነጋገር አለባቸው። የማህበራዊ ሰራተኛ፣ የጉዳይ ሀላፊ ወይም የ Washington ግዛት ተወካይ ይህን ሊደርግ አይችልም።

### የገቢ ማስረጃ

ሰው ወይም ኩባንያ የገቢዎትን ማስረጃ ከፈለጉ IPOne ያነጋግሩ። ከቀጣሪዎት ማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ ወይም ጉዳይ ሀላፊ የገቢዎትን ማስረጃ ማግኘት አይችሉም።

ለደሞዝ ማረጋገጫ PPL እንዲያስኬደው የጽሁፍ መጠይቅ በፋክስ ወይም በ US ፖስታ ይላኩ።

- **መጠይቅዎትን** በፋክስ ለሚከተለው ይላኩ፡ **1-855-901-6904**. የደሞዝ ማረጋገጫ ምላሽዎን የሚያገኙበት በጣም ፈጣን መንገድ ይህ ነው።
- **የደሞዝ** ማረጋገጫ መጠይቅዎን በፖስታ ለሚከተለው ይላኩ፡

  Public Partnerships, LLC
  WA IPOne
  7776 S Pointe Pkwy W, Suite150
  Phoenix, AZ 85044

መጠይቅዎ ስም እና የገቢ ማረጋገጫው እንዲላክልዎት የሚፈልጉትን አድራሻ መያዝ አለበት። እንዲሁም የየትኛውን ወቅት የገቢ ማስረጃ እንደሚፈልጉ መግለጽ አለብዎት። ማረጋገጫው ተሰርቶ እና ለጠየቀው አካል እስኪደርስ ድረስ እባክዎ 2-5 የስራ ቀናት ይወስዳል። በስራው ሂደት እና በስራ ጫና ምክንያት በእዛው እለት ምላሽ ለሚሰጣቸውን መጠይቆች ዋስትና አንሰጥም።

## ስራዎትን ከለቀቁ

ለቀጣሪዎት መስራት ከማቆምዎት በፊት ቢያንስ ከሁለት ሳምንት በፊት የጽሁፍ ማስታወቂያ መስጠት አለብዎት። የማስታወቂያው ወቅት እስኪያበቃ ድረስ የተመደበልዎትን ስራ መስራት አለብዎት። ቀጣሪዎትን ብቻውን ያለ አስፈላጊ እገዛ መተው ህገወጥ ነው።

ማስታወቂያው ላይ የሚከተሉትን መጥቀስ አለብዎት፡

- ቀጣሪዎት እና/ወይም ህጋዊ ወኪሉ ይህ በጽሁፍ መሆን አለበት።
- የቀጣሪዎት የጉዳይ ሀላፊ ወይም የማህበራዊ ሰራተኛ።
- ቀጣሪዎት የጠየቀው ወይም ማሳወቅ ያለበት ሌላ ሰው ወይም ድርጅት።

## የስራ-አጦች ጥቅማ ጥቅም

የግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ስራዎት ካበቃ ወይም ቅጥርዎት ለተሰነ ወቅት ከተቋረጠ የቅጥር ደህንነት መምሪያ ጋር ለስራ-አጥ ጥቅማ ጥቅም ማመልከት ይችላሉ (እንዲሁም የስራ-አጥ መድህን ተብሎ ይጠራል)። የስራ-አጥ ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት የቅጥር ደህንነት መምሪያ ማንኛውንም ደንብ ማሟላት አለብዎት። ማመልከቻው ከተሞላ በኋላ እራስዎን የ Washington ግዛት ግለሰብ አገልግሎት ሰጪ ብለው ይግለጹ። ባለጉዳይዎ ቀጣሪዎ ነው፤ ሆኖም ለስራ አጥነት ብቁ መሆን ለመወሰን የሚያገለግለው ታሪክዎ እና ገቢዎ የሚመጣው ከ IPOne ነው።



# ጥቃትን የማሳወቅ ግዴታ

ለጥቃት የተጋለጠ አዋቂ ሰው ወይም ልጅ እየተጎዳ ነው ብለው ከጠረጠሩ ወዲያው የማሳወቅ የህግ ግዴታ አለብዎት፡፡

## ለጥቃት የተጋለጠ አዋቂ ሰው ማን ነው?

እድሜው 60 እና ከዛ በላይ የሆነ እራሱን መንከባከብ የማይችል አዋቂ ሰው ለጥቃት የተጋለጠ አዋቂ ሰው ይባላል፡፡ ሌሎች ለጥቃት ተጋላጭ አዋቂ ሰዎች ማለት፡

- ህጋዊ ሞግዚት ያለው አዋቂ ሰው
- የእድገት ውስንነት ያለው አዋቂ ሰው
- በረዥም ግዜ የእንክብካቤ ቦታ ወይም አዋቂ ቤተሰብ ቤት ውስጥ የሚኖር አዋቂ ሰው
- የቤት ውስጥ እንክብካቤ ወይም የግል እንክብካቤ አገልግሎት የሚያገኝ አዋቂ ሰው

## ጥቃት ምንድን ነው?

- ለጥቃት የተጋለጠ አዋቂ ሰው ላይ ሆን ብሎ ህመም ስቃይ እና/ወይም ጉዳት ማድረስ
- አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ወሲባዊ ወይም ማሰሪያ እቃዎችን አለአግባብ መጠቀም ሊሆን ይችላል
- ለጥቃት የተጋለጠ አዋቂ ሰውን መተው፣ ችላ ማለት፣ ጉልበት መበዝበዝ ወይም የገንዘብ መበዝበዝ ሊሆን ይችላል
- ለጥቃት የተጋለጠ አዋቂ ሰው እራሱ በራሱ ላይ የሚያደርገው ችላ ማለት ሊሆን ይችላል

ለጥቃት የተጋለጠ አዋቂ ሰው ጥቃት እየደረሰበት እንደሆነ ካመኑ ወይም ከጠረጠሩ የአዋቂ ሰው ጥበቃ አገልግሎት (APS) ጋር ይደውሉ፡፡

## የተጠረጠረን ጥቃት ማሳወቅ

### የተጠረጠረ አዋቂ ሰው ጥቃትን ለማስመዝገብ፡

ኦንላይን በሚከተለው ያሳውቁ፡ www.dshs.wa.gov/altsa/home-and-community-services/report-concerns-involving-vulnerable-adults

ክልል 1
የ **APS** መገኛ ቁጥር፡ 1-800-459-0421 (TTY) 509-568-3086
Spokane, Grant, Okanogan, Adams, Chelan, Douglas, Lincoln, Ferry, Stevens, Whitman, Pend Oreille, Yakima, Kittitas, Benton, Franklin, Walla Walla, Columbia, Garfield, Asotin, Klickitat

ክልል 2
የ **APS** መገኛ ቁጥር፡ 1-866-221-4909 (TTY) 1-800-977-5456
Snohomish, Skagit, Island, San Juan, Whatcom, King

ክልል 3
የ **APS** መገኛ ቁጥር፡ 1-877-734-6277 (TTY) 1-844-433-5367
Bremerton, Pierce, Thurston, Mason, Lewis, Clallam, Jefferson, Grays Harbor, Pacific, Wahkiakum, Cowlitz, Skamania, Clark

### የተጠረጠረ የልጅ ጥቃት ለማስመዝገብ፡

ክልል 1
1-800-557-9671
Asotin, Garfield, Whitman, Adams, Grant, Douglas, Chelan, Okanagan, Ferry, Stevens, Pend Oreille, Spokane, Lincoln counties

ክልል 2
1-855-420-5888
Kittitas, Yakima, Klickitat, Benton, Franklin, Walla Walla, Columbia counties

ክልል 3
1-866-829-2153
Whatcom, Skagit, Snohomish, Island, San Juan counties

ክልል 4
1-800-609-8764
King county

ክልል 5
1-888-713-6115
Pierce and Kitsap counties

ክልል 6
1-888-713-6115
Clallam, Jefferson, Mason, Grays Harbor, Thurston, Lewis, Pacific, Cowlitz, Clark, Skamania, Wahkiakum countie

### የእንክብካቤ ቦታዎች ላይ ያለዎትን ስጋቶችን ማሳወቅ

ስለአዋቂ ቤተሰብ ቤት፣ እገዛ ያለው የመኖሪያ ቦታ ወይም የመንከባከቢያ ቤት ያለዎትን ስጋቶችን ለቅሬታ ሰሚ ክፍል (CRU) ያሳውቁ። ኦንላይን ወይም በስልክ ማሳወቅ ይችላሉ።

ኦንላይን ያሳውቁ

www.dshs.wa.gov/altsa/home-and-community-services/report-concerns-involving-vulnerable-adults

የቅሬታ ሰሚ ክፍል ብሄራዊ መገኛ ቁጥር

1-800-562-6078 (TTY) 1-800-737-7931

## የምንጮች አጭር መምሪያ

### የስልጠና እና የ HCA ማስረጃዎች

- DSHS: www.dshs.wa.gov/altsa/long-term-care-professionals-providers
- የጤና መምሪያ: www.doh.wa.gov/LicensesPermitsandCertificates/ProfessionsNewReneworUpdate/HomeCareAide
- Prometric: www.prometric.com/en-us/clients/wadoh/Pages/landing.aspx

### ግለሰብ PROVIDERONE

- Washington የጥሪ ማዕከል፡ 1-844-240-1526
- ኢሜል: pplwaipone-cs@pcgus.com
- Public Partnership LLC Washington IPOne ግብአቶች፣ የስልጠና መረጃ እና ሌላም: www.publicpartnerships.com/programs/washington/ipone/
- አጠቃላይ መረጃ: www.ipone.org
- ግለሰብ ProviderOne ፖርታል: https://ipone.publicpartnerships.com/login.aspx

## SEIU 775

- የህብረት ጥቅሞች: www.seiu775.org
- የአባል ምንጭ ማዕከል ኢሜል: mrc@seiu775.org
- የአባል ምንጭ ማዕከል ስልክ ቁጥር: 1-866-371-3200

*በሌላ ቋንቋ ሰው ለማናገር ከዝር ባለው ሰንጠረዥ ላይ በሚገኙት የውስጥ መስመሮች ይደውሉ፡፡*

## SEIU 775 የጥቅማ-ጥቅም ቡድን

- የስልጠና መስፈርት እና አማራጭ: www.myseiubenefits.org
  - የጤና ጥቅማጥቅም መግለጫ እና አማራጭ: www.myseiubenefits.org
  - አስተማማኝ ጡረታ መግለጫ እና በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች: www.myseiubenefits.org
- የአባል ምንጭ ማዕከል ኢሜል: mrc@seiu775.org
- የአባል ምንጭ ማዕከል ስልክ ቁጥር: 1-866-371-3200

*በሌላ ቋንቋ ሰው ለማናገር ከዝር ባለው ሰንጠረዥ ላይ በሚገኙት የውስጥ መስመሮች ይደውሉ፡፡*

| ቋንቋ | የውስጥ መስመር | ቋንቋ | የውስጥ መስመር |
|---|---|---|---|
| ሩሲያንኛ | 411 | ሶማሊኛ | 431 |
| ዩክረይንኛ | 412 | ዓረብኛ | 432 |
| የስፔን ቋንቋ | 413 | ማንዳሪን | 423 |
| የኮሪያ ቋንቋ | 421 | የቬትናም ቋንቋ | 422 |
| ካንቶኔስ | 424 | ስዋሂሊ | 433 |
| ታጋሎግ | 442 | የካምቦዲያ ቋንቋ | 441 |

## የቡድን መሪ/አስተማሪ

**SEIU 775 ጥቅማ-ጥቅም ቡድን** የተረጋገጠ HCA የቡድን መሪ/አስተማሪ በመሰረታዊ ስልጠና በተገኘ እውቀት እና ችሎታ ላይ በራስ መተማመን እንዲያዳብሩ ይረዳል፡፡

- Peer Mentor: www.myseiubenefits.org/peermentors/
- የቡድን መሪ/አስተማሪ ስልክ ቁጥር: 1-855-803-2095
- የቡድን መሪ/አስተማሪ ኢሜል: Peer.Mentorship@myseiubenefits.org

የቡድን መሪ/አስተማሪ ቦታዎች ከጊዜ ጊዜ ክፍት ይሆናሉ፡፡ የቡድን መሪ/አስተማሪነት ለማመልከት እባክዎ የሚከተለውን ይጎብኑ: www.myseiubenefits.org/work-with-us/፡፡ መካሪ ሆነው የሰሩበት ሰአት እንደ አጠቃላይ የስራ ሰአት አይቆጠርም፡፡ ለወደፊት የቡድን መሪ/አስተማሪነት እድል መመረጥ ከፈለጉ Peer.Mentorship@myseiubenefits.org ላይ ኢሜል ያድርጉ

## ለ GOVDELIVERY ይመዝገቡ፡

https://public.govdelivery.com/accounts/WADSHSALTSA/subscriber/new

በ"ዜና እና ግብአት" ስር በተጠቃሚ የተመራ ቀጣሪ ይምረጡ

ከእድገት ውስንነት አስተዳደር አዳዲስ ነገር እና መረጃ ማግኘት ከፈለጉ
https://public.govdelivery.com/accounts/WADSHSDDA/subscribers/new

## የ CDE ድህረ-ገጽ ይመልከቱ፡

www.dshs.wa.gov/altsa/cde



መግለጫ መምሪያ ውስጥ የተካተተ መረጃ የቅጥር ውል አይደለም ወይም አያመላክትም እንዲሁም IP ሆነው ለቀጣይ ቅጥር መሰረት አይሆንም፡ ፡ በዚህ የመግለጫ መምሪያ ውስጥ የተካተተ መረጃ እና በውልዎት መካከል መቃረን ካለ ውልዎት ላይ ያለው ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

DSHS ከሰዎች ጋር ውል በማድረግ ወይም በማገልገል ሂደት በዘር፣ ቀለም፣ ብሄር፣ ጾታ፣ የጾታ መለያ፣ የጾታ መገለጫ፣ የወሲብ ዝንባሌ፣ እድሜ፣ ሀይማኖት፣ ኀሳ፣ የትዳር ሁኔታ፣ አካል ጉዳተኝነት ወይም የ Vietnam ዘመን የውትድርና ሁኔታ ወይም ማንኛውም የስሜት ህዋስ፣ የአዕምሮ ወይም የአካል ጉዳት መኖር ምክንያት መድልኦ አያደርግም፡፡

CDE የ IP ቅጥር እና ስራዎች ሲጀምር ይህ ሰነድ በተጠቃሚ
የተመራ ቅጥር ይተካል፡፡

ለበለጠ መረጃ እባክዎ www.dshs.wa.gov/altsa/cde ይጎብኙ፡፡

Washington State
Department of Social & Health Services

*Transforming lives*

DSHS 22-221 AM (Rev. 5/19) Amharic